የኢትዮጵያ የ2012/2013 የሰብዓዊ መብቶች ሪፖርት

አጭር ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፑብሊክ ናት። የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢሕአዴግ) በመባል የሚታወቀው በብሄር የተደራጁ አራት ድርጅቶች ቅንጅት ታኅሳስ 2012 በብልጽግና ፓርቲ እስኪተካ ድረስ መንግሥትን ይቆጣጠር ነበር።በ2007 በተካሄደው አጠቃላይ ምርጫ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር እና አጋር ድርጅቶች 547 የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ፓርላማ) መቀመጫዎችን በሙሉ አሸንፈው ግንባሩ በተከታታይ ለአምስተኛ ጊዜ ለተጨማሪ የአምስት ዓመት የሥልጣን ዘመን በቃ። በ2010 የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ እየገነገነ የመጣውን የወጣቱን የለውጥ ፍላጎት ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲቻል የፖለቲካ ማሻሻያዎችን ለማፋጠን በሚል ምክንያት ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው እንደሚለቁ አስታወቁ። ምክር ቤቱም እነዚህን ማሻሻያዎች እንዲመሩ አቢይ አህመድ አሊን ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ መረጠ ።ጠቅላይ ሚኒስትር አቢይ የብልጽግና ፓርቲ መሪ ናቸው ።

ብሔራዊ እና ክልላዊ የፖሊስ ኃይሎች ሕግን እና ሥርዓትን የማስከበር ኃላፊነት ሲኖራቸው፣ አንዳንድ ጊዜ የኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ኃይል የአገር ውስጥ ጸጥታ የማስከበር ድጋፍ ያደርጋል። የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ተጠሪነቱ ለሰላም ሚኒስቴር ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ መከላከያ ኃይል ተጠሪነቱ ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር ነው። የክልል መንግሥታት (ከአሜሪካ ግዛቶችጋር ተመሳሳይነት ያላቸው) የክልል የጸጥታ ኃይሎችን ይቆጣጠራሉ፤ እነዚህ የፀጥታ ኃይሎች ከፌዴራል መንግሥት ቁጥጥር ነፃ ናቸው። ሲቪል ባለሥልጣናት የጸጥታ ኃይሎችን በበላይነት ይቆጣጠራሉ። ሁሉም የጸጥታ ኃይሎች አባላት የተወሰኑ በደሎችን ፈጽመዋል።

የአቢይ ወደ ሥልጣን መምጣት በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ አዎንታዊ ለውጦችን አስከተለ። መንግሥት ቀደም ሲል በአገር ክህደት የተከሰሱ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ከወንጀል ፍረጃ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ፣ የተቃዋሚ መሪዎች እንዲመለሱና የፖለቲካ እንቅስቃሴዎችን እንዲጀምሩ ጥሪ አቅርቧል ፣እንዲሁም ሰላማዊ ሰልፎችን ፈቅዷል፤ ከተጽዕኖ ነጻ የሆኑ

የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የሚዲያ ተቋማት እንዲመሰረቱ አድርጋል፤ አፋኝ በሆኑ ሕጎች ላይ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። የፖለቲካ ምህዳሩ መስፋት የራሱን ተግዳሮቶች ይዞ መጣ። ማሻሻያዎች እየተካሄዱ ያሉት የጸጥታ ዘርፉን ጨምሮ ደካማ ተቋማት ባሉበት ሁኔታነው። ከብሔር ማንነት ጋር ተያያዥ የሆኑ ውጥረቶች ቀጥለው በአንዳንድ አካባቢዎች ከፍተኛ ጥፋት ደርሷል። አብዛኞቹ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች የተፈጸሙት ዜጎች በዜጎች ላይ በሚያደርሷቸው ጥቃቶች ነው።

ጥቅምት 25 በኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ኃይል እና በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ የክልል የጸጥታ ኃይል መካከል የተከሰተው ግጭት በሰሜናዊው የትግራይ ክልል የተራዘመ ጦርነትን ያስከተለ ሲሆን፣ አሳሳቢ እና መጠነ ሰፊ የመብት ጥሰት ሪፖርት እየተደረገ ይገኛል። በዓመቱ መጨረሻ ገደማ፣ ከዋና ከተማዋ መቀሌ በስተቀር አብዛኛው የትግራይ ክፍል ያለው ተደራሽነት እጅግ የተገደበ በመሆኑ፣ ሪፖርት ማግኘት ካለመቻሉም ሌላ፣ በሰብዓዊ መብት ላይ የሚፈጸሙ ጥሰቶችን መጠን ለማረጋገጥ አሰቸጋሪ አድርጎታል።

ከጉልህ የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮች መካከል፡- በጸጥታ ኃይሎች እና በግለሰቦች በሕገወጥ እና በዘፈቃደ የሚፈጸሙ ግድያዎች፤ ባልታወቁ ታጣቂዎች በግዳጅ መሰወር፤ ማሰቃየት እና በመንግሥት የሚፈጸም ጭካኔ፣ ኢ-ሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን የሚነካ አያያዝ ወይም ቅጣት፣ አስከፊ እና ለሕይወት አደገኛ የሆኑ የእስር ሁኔታዎች፤ በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋልና እስር ፣ በውስጥ ግጭት ምክንያት ከፍተኛ በደሎች እና የዜጎች መገደል፣ ጋዜጠኞችን ማዋከብ፣ በይነ መረብ እና የማኅበራዊ ሚዲያ ገጾችን መዝጋትን ጨምሮ; ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የሚዲያ እና የበይነ መረብ የመጠቀም መብት በእጅጉ መገደብ፣ ሰላማዊ ስብሰባ የማድረግ እና የመደራጀት መብት ላይ ጣልቃ መግባት፣ ከፍተኛ የሙስና ተግባር፣ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች ላይ ምርመራ አለማካሄድ እና የተጠያቂነት አለመኖር፤ በአናሳ ብሔሮች ላይ ያነጣጠረ የኃይል ድርጊት መፈጸም ወይም ማስፈራራት፤ የተመሳሳይ ጾታ ግንኙነትን ሕገ ወጥ የሚያደርጉ ሕግጋት መኖራቸው እና በነዚህ ሕግጋት መጠቀም ይጠቀሳሉ።

አንዳንድ ጊዜ መንግሥት የሰብዓዊ መብት ጥሰት በሚፈጽሙ ባለሥልጣኖች ላይ ክስ ያለመመሥረት፣ በዚህም የተቋማዊ አቅም ማነስ ምክንያት በዳዮች በህግ ሳይጠየቁ

እንዲቀሩ ሆኗል። የአብይ አስተዳደር በደህንነት ሃይሎች እና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት በማሻሻል፣ ተጠያቂነት ያለው ሥርዓት በማስፈን በኩል አዎንታዊ እርምጃዎችን ወስዷል። በሰኔ ወር የጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት እና መንግስታዊው የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በጸጥታ ኃይሎች ስለተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች አምነስቲ ኢንተርናሽናል ተፈጽመዋል ያላቸውን ጥሰቶች መርምረዋል። እንዲሁም አስተዳደሩ ከዚህ ቀደም በመሰብሰብ ነጻነት፣ በፖለቲካ እስረኞች እና ግላዊ መብት ላይ ስለሚደረጉ ጣልቃ ገብነቶች ይቀርቡ በነበሩ ሪፖርቶች ላይ ተመስርቶ ምላሽ ሰጥቷል። በነሐሴ ወር መገባደጃ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና መንግሥታዊ ያልሆኑ የሰብዓዊ መብት ድርጅቶች በኦሮሚያ ክልል በ40 አካባቢዎች ሰኔ 22 ቀን የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳን ግድያ ተከትሎ በማንነት ላይ ተመስርቶ የተፈጸሙ ግድያዎችን እንዲያጣሩ መርማሪዎች አሰማርተዋል።

በልዩ ኃይሎች፣ በአማጺያን እና በወጣት ቡድኖች የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ነበሩ። ጥቅምት 30 ቀን በማይካድራ፣ ትግራይ በተፈጸመ ጥቃት የትግራይ ወጣቶች ቡድን በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ክልላዊ የጸጥታ ኃይል ድጋፍ በግምት 600 ያህል ሰዎች መግደሉን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የቅድሚያ ምርመራ አረጋግጧል። አምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደዘገበው ጥቃቱን የፈጸመው የሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ ክልላዊ የጸጥታ ኃይል ነው። አንድ የሀገር ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ቡድን እንደገለፀው ሰኔ 22 እና 23 የወጣቶች ቡድን በኦሮሚያ ባሌ እና አርሲ ዞኖች በሚገኙ መንደሮች ላይ ጥቃት ፈጽሟል። የሃጫሉ ሁንዴሳን ሞት ተከትሎ ፌዴራል ፖሊስ በዚህ ጥቃት ውስጥ በመሳተፋቸው ወይም ጥቃቱን ባለመከላከላቸው 1,500 የክልል ባለሥልጣናትን አስሯል። ተገንጣይ የኦሮሞ ነጻነት ታጣቂ ቡድን - ሸኔ በምዕራብ፣ በማዕከላዊ እና በደቡባዊ የኦሮሚያ ዞኖች ካሉት ኣንጃዎቹ ጋር በመሆን ሲቪሎችን እና የመንግሥት ባለሥልጣናትን ገድሏል።

ክፍል 1፡- የሰውን ልጅ በሰውነቱ ማክበር፣ ከዚህ ከሚከተሉት እና ከሌሎችም ነጻ መሆን

ሀ. በዘፈቀደ ሕይወትን ማሳጣት፣ እንዲሁም ሌሎች ከሕግ ውጪ እና በፖለቲካ ምክንያት የሚፈጸሙ ግድያዎች

መንግሥት እና ወኪሎቹ የዘፈቀደ እና ሕገወጥ ግድያዎችን ስለመፈጸማቸው በርካታ ሪፖርቶች ነበሩ። የጸጥታ ኃይሎች በሲቪሎች ላይ ከመጠን ያለፈ ኃይል መጠቀማቸውን አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በሪፖርታቸው አመልክተዋል። ሌሎች ክስተቶች ደግሞ በዓለም ዓቀፍ አካላት በመመርመር ላይ ይገኛሉ። የፌዴራል ፖሊስ በአባላቱ የተፈጸሙ የወንጀል ጥሰቶችን የሚመረምር ውስጣዊ የምርመራ ክፍል ነበረው። ፤ የውስጥ ክፍሉ በፖሊሶች ላይ ስለሚጣሉ ቅጣቶች ያስተላለፋቸው ውሳኔዎች በምሥጢር ይያዛሉ።

በውስጡ የወታደር ፖሊስ ክ/ጦር ያለው የኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ሰራዊት ወታደራዊው የምርመራ ቡድን ለወታደራዊ ዓቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ሪፖርት አቅርቧል። ወታደራዊ ፖሊሱ ከምርመራዎቹ ያገኘውን ማስረጃ ለዓቃብያን ህግ እና ለመከላከያ ጠበቆች አስተላልፏል። የኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ሰራዊት ዓቃቤ ህግ ምርመራዎቹን አካሂዶ ክሶቹን በወታደራዊ ፍርድ ቤት አሰምቷል።

ጥር 12 ቀን አንድ የጸጥታ ሹም በምዕራብ ኦሮሚያ ሙጊ በተባለ ሥፍራ በሱቁ ውስጥ የነበረ አንድ የ20 ዓመት ወጣት ላይ መተኮሱ ሪፖርት ተደርጓል። ጥር 13 ቀን ያልታወቁ የጸጥታ ሹማምንት ከሙጊ ከተማ ወጣ ብላ በምትገኝ አነስተኛ ከተማ አምስት ወጣቶችን አስረው ፣ በግል መኖሪያ ቤት ውስጥ ከመረመሯቸው በኋላ እንደገደሏቸው የአካባቢው ጋዜጠኛ ሪፖርት አድርጓል። እነዚህን በደሎች የፈጸሙው የጸጥታ ኃይል የትኛው እንደሆነ ግልጽ አይደለም።

ነሐሴ 3 ቀን የክልል ልዩ ኃይሎች በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦችክልላዊ መንግሥት፣ ወላይታ ዞን፣ ሶዶ ከተማ ውስጥ ከተቃውሞ ሰልፈኞች ጋር ተጋጩ። የዞኑን ዋና አስተዳዳሪ ዳጋቶ ኩምቢን እና የወላይታ ብሔራዊ ንቅናቄ ተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን ጨምሮ ከክልሉ አመራሮች መካከል 28ቱ መታሰራቸውን በመቃወም ወጣቶች መንገድ ከዘጉ እና የመኪና ጎማዎችን ካቃጠሉ በኋላ የጸጥታ ኃይሎች 17 ሰዎችን መግደላቸው በመገናኛ ብዙኃን ተዘግቧል።

ነሐሴ 21 ቀን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የጸጥታ ኃይሎች በአሳሳ፣ በሻሸመኔ፣ በባሌ ሮቤ፣ በጊኒር፣ በአሰቦት፣ በጭሮ እና በአወዳይ ተቃዋሚዎችን ስለመግደላቸው ማስረጃ እንዳለው በመግለጽ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን መንግሥት እነዚህን ክስተቶች የሚመረምር ገለልተኛ አካል እንዲያቋቁም ጥያቄ አቅርቧል።

ግንቦት 21 ቀን በትግራይ ክልል ዋና ከተማ መቀሌ የአከባቢውን ሚሊሻ አባል ደመወዝ አስመልክቶ በተነሳ ውዝግብ አንድ የአከባቢው የሚሊሻ አባል አንዲትን ሴት በጥይት ተኩሶ ገድሏል። ከዚያ በኋላ ሚሊሺያው ራሱን በጥይት ቢመታም ሕይወቱ ተርፏል።

ግንቦት 21 ቀን የቀድሞ ኦሮሞ ነጻ አውጪ ሰራዊት - የታጣቂ ገንጣይ ቡድን ሸኔ (ኦነግ - ሸኔ) አባላት በምዕራብ፣ በማዕከላዊ እና በደቡባዊ ኦሮሚያ አንጃ ኃይሎች ያሉት በኦሮሚያ ክልል፣ ምዕራብ ወለጋ ዞን፣ ዋጋሪ ቡና በሚባል ሥፍራ አራት የመንግሥት ሠራተኞችን ገድሎ ሦስቱን ደግሞ አቁስሏል የሚል ዘገባ ቀርቧል። አራቱ የመንግሥት ሠራተኞች ከአጎራባች ቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ለተፈናቀሉ ሰዎች የግብርና አቅርቦቶች ለማድረስ ወደ ነጆ ከተማ በመጓዝ ላይ ነበሩ ።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል ጥቅምት 30 በምዕራብ የትግራይ ክልል በሚገኘው ማይካድራ ከተማ አንድ የታጣቂ ቡድን በርካታ ሲቪሎችን መግደሉን ዘግቧል። እንደ ዘገባው ከሆነ አብዛኞቹ ሟቾች የትግራይ ተወላጅ ያልሆኑ፣ በወቅቱ ለነበረው የጉልበት ሥራ ወደ ሥፍራው የሄዱ ሰዎች ናቸው። የአማራ ክልል ሚዲያ ኤጀንሲ በዘገባው ሟቾች በግምት 500 ይሆናሉ ብሏል። የጥቃቱ ፈጻሚዎች ማንነት ባይረጋገጥም እንኳን፣ ምሥክሮች እንዳሉት ገዳዮቹ ከሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ የክልል የጸጥታ ኃይል ጋር ግንኙነት ያላቸው ናቸው (ክፍል 1.ሰ.፤ የውስጥ ግጭት ተጠቂ የሆነውን ሰው ክብር ስለመጠበቅ የሚገልጸውን ክፍል ይመልከቱ)።

ለ. መሰወር

በመንግሥት ባለሥልጣናት ወይም በነሱ ሥም የተፈጸሙ መሰወሮች ስለመኖራቸው ሪፖርት የተደረገ የለም።

በታኅሳስ 2012 በግምት 17 የሚሆኑ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በምዕራብ ኦሮሚያ ክልል በታጠቀ ኃይል ታግተው ተወስደዋል። በዚህም ምክንያት መንግሥት 17 የኦነግ-ሸኔ አባላትን በሽብር ወንጀል ከሷል። በተጠርጣሪዎቹ ላይ የፍርድ ሂደት ከታኅሳስ ወር አንስቶ ቀጥሏል። በዓመቱ መጨረሻ የተሰወሩት ተማሪዎች ሁኔታ አልታወቀም። ።

ሐ. ማሰቃየት እና ሌላ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢ-ሰብዓዊ ወይም ክብርን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት

እንደዚህ አይነቶቹን እርምጃዎች ሕገ መንግሥቱ የሚከለክል ቢሆንም፤ የደህንነት ባለሥልጣናት እስረኞችን እንደሚያሰቃዩ እና በደል እንደሚያደርሱባቸው ሪፖርቶች ይሳያሉ።

ግንቦት 21 የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በኦነግ-ሸኔ አካባቢዎች የማሰቃየት ተግባር መፈጸማቸውን አምነስቲ ኢንተርናሽናል ዘግቧል። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የዓቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ሪፖርቱን ተመልክተው ሚዛናዊነት የጎደለው ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል።

ኮንዳክት ኢን ይኤን ፊልድ ሚሽንስ ድረገጽአማካኝነት እ.ኤ.አ. በ2018 አንድ ሪፖርት ቀርቦ ነበር፤ እንደ ዘገባው በተባበሩት መንግሥታት የሰላም ማስከበር ተልዕኮ የተመደበ የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ኃይል አባል በወሲብ ብዝበዛ ተሳትፏል። በጥቅምት ወር የተባበሩት መንግሥታት ይህንን ክስ በማስረጃ ለማረጋገጥ በመቻሉ፤ የሰላም አስከባሪ ኃይል አባሉ ወደ አገሩ እንዲመለስ ተደርጓል። ሆኖም ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ስለወሰደው የተጠያቂነት እርምጃ በዓመቱ መጨረሻ መረጃ አልሰጠም።

የጸጥታ ኃይሎች ለሚፈጽሟቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች አንዳንድ እርምጃዎች ቢወሰዱም እንኳን፣ ጥፋተኞች ተገቢውን ቅጣት ሳያገኙ የሚቀሩበት ሁኔታ አሁንም ቀጥሏል። እንዲህ ያሉ ሰዎች በፍርድ ቤት ቀርበው መከሰሳቸው እና የፍርድ ሂደታቸው

ግልጽነት ስለሚጎድል በዚህ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ መሻሻል መኖሩን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ አድርጎታል።

እስር ቤት እና የማቆያ ማዕከል ሁኔታዎች

የእስር ቤት እና ቅድመ ክስ የማቆያ ቦታዎች ሁኔታዎች እጅግ አስቸጋሪ እና አንዳንዶቹ እንዲያውም ለሕይወት አስጊ ሆነው ታይተዋል። ካጋጠሙ ችግሮች መካከል እስር ቤቶቹ ካላቸው የመያዝ አቅም በላይ በእስረኞች መጨናነቃቸው እንዲሁም በቂ ምግብ፣ ውሃ፣ ንጽሕናና የሕክምና እንክብካቤ አለመኖር ይጠቀሳሉ። ፍርድ ቤት ከመቅረባቸው በፊት እስረኞች የሚቆዩባቸው አብዛኛውን ጊዜ በፖሊስ ጣቢያዎች ሲሆን፣ የአንዱ ሁኔታ ከሌላው እጅግ መለየቱ እንዲሁም የንጽሕናው ዝቅተኛነት በዘገባዎች ተመልክቷል።

<u>አካላዊ ሁኔታዎች</u>፡- ከፍተኛ መጨናነቅ የተለመደ ነው፤ በተለይ በእስር ቤት የመኝታ ክፍሎች። የእስር ቤት ክፍሎች ጠባቦች እና የተጨናነቁ ናቸው። ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች እንደዘገቡት በግምት 430 ካሬ ጫማ ስፋት ወዳላቸው ክፍሎች አነስተኛ ብርሃን ብቻ እንዲገባ የሚያስችሉ አነስተኛ መስኮቶች ያሏቸው የእስር ቤት ክፍሎች መኖራቸው የተለመደ ሆኖ በአንዱ ክፍል ውስጥ አስከ 38 ታራሚዎች ይታሰራሉ። የእስር ቤቱ ኃላፊዎች አንዳንድ ጊዜ ወጣት ጥፋተኞችን ከአዋቂዎች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ያስራሉ። የእስር ቤቱ አስተዳዳሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ወንዶችን እና ሴቶችን ለይተው የሚያስሩ ቢሆንም በአንዳንድ ማዕከሎች ውስጥ መደባለቅ ተከስቷል።

መንግሥት ለምግብ፣ ለውሃ እና ለጤና እንክብካቤ በቀን በግምት ዘጠኝ ብር ($0.23) የመደበ ሲሆን፣ ይህ የገንዘብ መጠን በአገሪቱ እንደየአካባቢውይለያያል። በርካታ እስረኞች ከቤተሰቦቻቸው በየዕለቱ ምግብ ስለሚቀርብላቸው ወይም በአካባቢው ካሉ የምግብ አገልግሎት ሰጪዎች ስለሚገዙ የመንግስትን የአቅርቦት ክፍተት ይሸፍናሉ። ሪፖርቶች እንዳመለከቱትየእስር ቤት ኃላፊዎች አንዳንድ እስረኞች ከቤተሰቦቻቸው ምግብ እዳያገኙ ክልከላ አድርገዋል። አንዳንድ ቤተሰቦች ዘመዶቻቸው የት እንደታሰሩም አያውቁም። ሕክምና በፌደራል እስር ቤቶች አስተማማኝ አይደለም፤ በክልል እስር ቤቶች ደግሞ ከሞላ ጎደል የማይታሰብ ነው። አንዳንድ ጊዜ አካላዊ ጥቃት ከደረሰ በኋላ የሚሰጥ የሕክምና እርዳታ በቂ አይደለም።

ለእስረኞች የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት በእጅጉ የተገደበ ነበር። የውሃ እጥረት የንጽህና ጉድለት እንዲንሰራፋ አድርጓል፤ አብዛኞቹ እስር ቤቶች ተገቢ የንጽሕና መስጫ ተቋማት የሏቸውም። ብዙዎች ታሳሪዎች ከፍተኛ የጤና ችግር እያለባቸው ያገኙት ሕክምና አነስተኛ ነው፤ አሊያም ምንም ዓይነት ሕክምና አልተደረገላቸውም። የእስር ቤቱ ኃላፊዎች አንዳንድ እስረኞች አስፈላጊውን ሕክምና እንዳያገኙ ክልከላ እንዳደረጉ የሚገልጹሪፖርቶች ነበሩ።

በይፋ በሚታወቅ እስር ቤት ካልሆነ በቀር ሰዎችን በማናቸውም ስፍራ ማሰር በሕግ የተከለከለ ነው። ሆኖም ግን የአካባቢ ሚሊሻዎች እና ሌሎች መደበኛ እና ኢመደበኛ ሕግ አስከባሪ አካላት ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ይፋዊ ያልሆኑ እስር ቤቶች ነበሯቸው።

የአርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳን ሞት ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል በግምት 9500 የሚሆኑ ሰዎች ከማንነት ጋር በተያያዘ ዓመፅ እና በንብረት ውድመት ተጠርጥረው ታስረዋል (ክፍል 6፣ የብሔራዊ/የዘር/የብሔር አናሳ ጎሳዎች የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)። የክልል ባለሥልጣናት በኋላ እንደገለጹት ከታሰሩት መካከል በግምት ግማሽ ያህሉ ተለቀዋል። መስከረም 16 ከዓመፅ ድርጊቱ ጋር በተያያዘ 5,728 ሰዎች ላይ ክስ መመስረቱን የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት አሳውቋል። በእስር ቤቶች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ታሳሪዎች በመኖራቸው፣ በእነዚህ ተቋማት የኮቪድ-19 ስርጭት አሳሳቢ ሆኗል። የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን በታሳሪዎች መካከል አካላዊርቀት እንዲኖር ለማድረግ፣ ትምህርት ቤቶችን እንደ ጊዜያዊ እስር ቤቶች እንደሚጠቀም በመግለጽ ምላሽ ሰጥቷል።

<u>አስተዳደር</u>፡- በእስር ቤቶች የጥበቃ አባላት እንግልት የደረሰባቸው እስረኞች ቅሬታዎቻቸውን ለእስር ቤቱ አስተዳዳሪዎችም ሆነ ለእምባ ጠባቂ አካላት ለማሳወቅ እንዳይችሉ መደረጉ ተዘግቧል። በአንዳንድ እስር ቤቶች የሕግ ድጋፍ መስጫ ማዕከላት አሉ። በክልል ደረጃ እነዚህ ማዕከላት ከፍርድ ቤቶች፣ ከእስር ቤት እና ከሌሎች የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ጥሩ የሥራ ግንኙነት ነበራቸው ። የእስር ቤት ኃላፊዎች ለአንዳንድ ታሣሪዎች ያለሳንሱር አቤቱታዎቻቸውን ለፍርድ ቤት እንዲያቀርቡ ቢፈቅዱላቸውም፣ አንዳንድ ጊዜ ፍርድ ቤቶች እነዚህን መሰል አቤቱታዎች ለመስማት ፈቃደኞች ሳይሆኑ ቀርተዋል።

ሕጉ እስረኞች እንዲጠየቁ ይፈቅዳል። ነገር ግን ባለሥልጣናት አንዳንድ ክስ የቀረበባቸው ተከሳሾች ከጠበቆቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ክልከላ አድርገውባቸዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ፖሊሶች በቀጠሮ ላይ ያሉ እስረኞች የቤተሰብ አባላት እና ጠበቆቻቸውን ጨምሮ ከጎብኚዎቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ክልከላ አድርገዋል። የሀገሪቱ የማረሚያ ቤት ደንቦች እንደሚገልፁት፣ በሽብር ወንጀል የተከሰሱ ታሳሪዎች ጠበቆች በቀን መጠየቅ ወይም ማነጋገር የሚችሉት አንድ እስረኛ ብቻ ነው፤ ያውም በረቡዕ እና በዓርብ ቀናት ብቻ። የማረሚያ ቤት ኃላፊዎች በሽብር ድርጊት የተከሰሱ ሰዎች ከቤተሰብ አባላት ጋር እንዳይገናኙ እገዳ ጥለዋል።

የማረሚያ ቤት ኃላፊዎች ታራሚዎች የኃይማኖት ሥርዓት እንዲፈጽሙ ቢፈቅዱም፣ ይህ ፈቃድ ግን በማረሚያ ቤቶች መካከል እንዲሁም በአንድ ማረሚያ ቤት ውስጥ አንኳን ከክፍል ክፍል የተለያየ ነው። የማረሚያ ቤት ኃላፊዎች ለታራሚዎች የሚሆን በቂ የጸሎት ቦታ ከልክለዋል የሚል አቤቱታ ቀርቧል።

<u>ገለልተኛ ቁጥጥር</u>፡- በዓመቱ ውስጥ ዓለም ዓቀፍ የቀይ መስቀል ኮሚቴ (ICRC) የዓመታዊ መደበኛ ሥራው አካል በሆነ መልኩ በመላው አገሪቱ የሚገኙ 51,000 ታራሚዎችን በወህኒ ጎብኝቷል።

የክልል ባለሥልጣናት ሦስተኛ ወገኖች በሌሉበት የመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች ከታራሚዎች ጋር እንዲገናኙ ፈቅደዋል። የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የፌዴራል እና በክልል ማረሚያ ቤቶችን ቅኝት በማድረግ ከማረሚያ ቤት አስተዳዳሪዎች እና ከታራሚዎች ጋር ቃለ ምልልስ አድርገዋል። ጀስቲስ ፎር ኦል - ኢትዮጵያ ፕሪዘንስ ፌሎሺፕ በአገሪቱ ዙሪያ በርከት ያሉ ማረሚያ እና ማቆያ ሥፍራዎችን ለመጎብኘት ችለዋል።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና ዓቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ታዋቂው አርቲስት ሃጫሉ ሁንዴሳ መገደሉን ተከትሎ የተፈጠረውን አለመረጋጋት እና ረብሻ አስተባብረዋል በሚል የታሰሩትን ታዋቂ ፖለቲከኞች ደህንነት የማጣራት ሥራ ሰርተዋል ። ከሐምሌ ፤ ጀምሮ ባለው አንድ ሳምንት፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እነ ጃዋር መሐመድ፣ እስክንድር ነጋ እና በቀለ ገርባን የመሳሰሉ ታዋቂ እስረኞችን ሁለት ጊዜ ጎብኝቷል።

ገለልተኛው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ታሳሪዎቹ በጥሩ ጤና ላይ እንደሚገኙ፣ በቤተሰቦቻቸው እንደሚጠየቁ እና ከተከላካይ ጠበቆቻቸው ጋር እንደሚገናኙ ዘግቧል።

<u>መሻሻሎች</u>፡- የካቲት 9 መንግሥት የፌዴራል ማረሚያ ቤት አዋጅን አወጣ፤ አዋጁ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ራሱን የቻለ ገለልተኛ አካል እንዲሆን እና ተጠሪነቱ ለዓቃቤ ሕግ እንዲሆን ይደነግጋል። ሁሉም እስረኞች ሰብዓዊ መብታቸው በተጠበቀ መልኩ መያዝ እንዳለባቸው ሆኖ መልሶ ለማቋቋም እንዲያግዝም ትምህርት እና የሙያ ስልጠና እንዲሰጣቸው፣ እስረኞች አልባሳት እና በቀን ሦስት ጊዜ ምግብ እንዲያገኙ፣ እንዲሁም በማረሚያ ቤቱ ውስጥ አዕምሮ ጤና ሕክምናን አካትቶ በነጻ የሕክምና እንክብካቤ እንደሚደረግላቸው ይደነግጋል። የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን በማኅበረሰብ መሪዎች (የኃይማኖት፣ የባሕል እና የሰብዓዊ መብቶች መሪዎች)፣ በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና በምክር ቤት ክትትል እና ቁጥጥር እንደሚደረግበት ይደነግጋል። እንዲሁም ታራሚዎች በማረሚያ ቤቱ በሚቆዩባቸው ጊዜያት "ሰብዓዊ ክብራቸውን እና ጤናቸውን በሚጠብቅ መልኩ መኖሪያ እንዲያገኙ" ይደነግጋል። አዋጁ ለመጀመሪያ ጊዜ ለታራሚዎች የዕድሜ ፣ የጾታ እና የስጋት ደረጃን መሠረት ያደረገ ምደባ እና ልየታ እንዲኖር ይደነግጋል።

ይህ ሕግ በማረሚያ ቤቱ የአሠራር ሥርዓት ለውጥእንዲመጣ አስችሏል። የማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን የራሱ በጀት እና ከሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች የእዝ ሰንሰለት ነበረው። ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ በቀጥታ ለፓርላማው ነበር። ታራሚዎች ተመልሰው ወንጀል ወደ መፈጸም እንዳይገቡ ኮሚሽኑ የራሱ የሥልጠና ማዕከላት፣ የትምህርት ፕሮግራሞች እና የመንጃ ፈቃድ ትምህርት መስጫ ከፍቷል። ኮሚሽኑ ወጪ ለመቀነስ እና በአካባቢው ማኅበረሰብ ሆስፒታሎች ላይ ያለውን ጥገኝነት ለመቀነስ የራሱን ሆስፒታሎች መገንባት ጀምሯል።

መ. በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋል ወይም እስራት

ሕገ መንግሥቱ እና የፌዴራል ሕጉ ሰዎች በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር እንዳይውሉ እና እንዳይታሰሩ ክልከላ ያደርጋሉ፤ እናም ማንኛውም ሰው በቁጥጥር ስር የመዋሉን ወይም የመታሰሩን ሕጋዊነት ፍርድ ቤት ቀርቦ የመገዳደር መብት አለው። መንግሥት እነዚህን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ አልተገበረም።

በቁጥጥር ስር የማዋል ሥርአቶች እና የታሳሪዎች አያያዝ
ARREST PROCEDURES AND TREATMENT OF DETAINEES

ሕገ መንግሥቱ እና ሕግ በቁጥጥር ስር የዋሉ ሰዎች በ48 ሰዓታት ውስጥ ወይም እንደ አካባቢው ሁኔታ እና የመገናኛ ዘዴዎች በሚፈቅዱት መጠን ከተገለጸው ጊዜ ብዙም ሳይዘገይ ፍርድ ቤት ቀርበው ክስ እንደሚመሰረትባቸው ይደነግጋሉ።ፍርድ ቤት ለመቅረብ የሚወስደው ጊዜ በ48 ሰዓቱ ውስጥ አይካተትም። በከባድ የወንጀል ድርጊት ለተጠረጠሩ ሰዎች ምርመራ በመካሄድ ላይ እያለ ክስ ሳይመሰረት ለ14 ቀናት በእስር እንዲቆዩ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል። ባለሥልጣናት በ14 ቀናቱ ጊዜ ውስጥ ማስረጃ ወይም አሳማኝ ምክንያት እንዲያቀርቡ ወይም ታሳሪው እንዲለቀቅ ፍርድ ቤቶች ጫና አሳድረዋል ። እንዲሁም ፖሊስ ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጠው ሲጠይቅ ለመገምገም እንዲያስችላቸው ፍርድ ቤቶች የፖሊስ የምርመራ መዝገቦችን ለማየት አጥብቀው ያሳስባሉ።

መጋቢት 28 ቀን ቀደም ብሎ በዘፈቀደ ማሰርን ይፈቅድ የነበረው የጸረ ሽብር ሕግ፤ በሌላ አዋጅ ተተካ። የጸረ ሽብር አዋጁ በዚህ ሕግ ሥር የተከሰሰ አንድ ተጠርጣሪ ወይም ተከሳሽ "በሕገ መንግስቱ፣ በዓለም ዓቀፍ ስምምንቶች [መንግሥት ባጸደቃቸው] እና ሌሎች የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎች መብቶችን በሚመለከቱ የአገሪቱ ሕግጋት መሠረት ጥበቃ ያገኛል" ሲል ይደነግጋል። የጸረ ሽብር ሕጉ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ባልተሰጠበት ሁኔታ ብርበራዎች እንዳይካሄዱ እና በግለሰቦች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች እንዳይጠለፉ ክልከላ ያደርጋል። አከራዮች የውጭ አገር ዜጎችን (ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎችን) ማንነት የተመለከተ መረጃ በ72 ሰዓታት ውስጥ ለፖሊስ እንዲሰጡ ይጠይቃል። ። በዚህ የነዋሪዎችን ተጠያቂነት በማስቀረት የሕጉን ተፈጻሚነት ወሰን በከፍተኛ ደረጃ የሚያጠብ ሲሆን፣ ይህንን ሕግ ባለማክበር ምክንያት የሚተላለፉትን ቅጣቶች ይቀንሳል። የጸረ ሽብር ሕጉ ፍርድ ቤት ሳያቀርቡ ለረጅም ጊዜ ማቆየትን ያስቀራል፤ ፍርድ ቤቶች ማናቸውንም ከሽብር ጋር ለተያያዙ ክሶች ቅድሚያ እንዲሰጡ ሥልጣን ይሰጣቸዋል።

ውጤታማ የዋስትና ሥርዓት ተግባራዊ ተደርጎ ነበር። በግድያ፣ በአገር ክህደት እና በሙስና ወንጀሎች ክስ ለተመሰረተባቸው ሰዎች ዋስትና የለም። በሌሎች ጉዳዮች ፍርድ ቤቶች ከብር 500 እስከ ብር 10,000 ($13 and $250) የዋስትና ገንዘብ የሚወስኑ ቢሆንም፣

አብዛኛዎቹ የአገሪቱ ዜጎች ይህንን ያህል የዋስትና ገንዘብ የመክፈል አቅም የላቸውም። በግል ጠበቃ ማቆም ለማይችሉ ተከሳሾች መንግሥት ጠበቃ ያቆምላቸዋል፤ ሆኖም ግን ተከሳሾች እንዲህ ያለውን አገልግሎት የሚያገኙት ጉዳዮቻቸው ወደ ፍርድ ቤት ሲደርሱ እንጂ በቅድመ የፍርድ ሂደት ወቅት አይደለም። አንዳንድ ጊዜ በአንድ ጉዳይ ለበርካታ ተከሳሾች (በአንድ ጉዳይ ለተከሰሱ) አንድ ጠበቃ ሲቆም ታይቷል።

<u>በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋል</u>፡- የጸጥታ ኃይሎች በዘፈቀደ እንደሚያስሩ ዘገባዎች አመልክተዋል

ግንቦት 5 በአዲስ አበባ "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ጥሳችኋል" እንዲሁም የአፍ መሸፈኛ አላደረጋችሁም በሚል በግምት 1,600 ሰዎች ታስረዋል። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የፊት መሸፈኛ አላደረጋችሁም በሚል ሰዎችን በዘፈቀደ ማሰሩ እንዲቆም አሳስቦ ፣ ስልቱም አላስፈላጊ እንደሆነ ገልጿል ። ሁሉም ታሳሪዎች በ72 ሰዓታት ጊዜ ውስጥ ተለቅቀዋል (በክፍል 1.ሐ. ያለውን ይመልከቱ)።

<u>የቅድመ ፍርድ ሂደትእስር</u>፡- ጉዳያቸው ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በእስር ላይ የቆዩ ታሳሪዎች ብዛት በመቶኛ እና አማካይ የእስር ጊዜያቸውን የሚያሳይ መረጃ የለም። ረጅም ጊዜ የፈጀ የክስ ሂደት፣ ከፍተኛ የታሳሪዎች ቁጥር፣ የፍትህ አካላት አቅም አናሳ መሆን እና የባለሙያዎች እጥረት የፍርድ ቤት ጉዳዮች እንዲጓተቱ፣ አንዳንድ ጊዜም ለዓመታት እልባት ሳያገኙ እንዲቆዩ ምክንያት ይሆናሉ።

<u>ታሳሪዎች በቁጥጥር ስር የመዋላቸውን ህጋዊነት በሚመለከት ፍርድ ቤት ቀርበው የመገዳደር ችሎታ፤ በዓመቱ</u> ከህግ ውጭ ስለመታሰር ከግለሰቦች ለፍርድ ቤት የቀረበ አቤቱታ አልነበረም። ከህግ ውጭ በቁጥጥር ስር ለዋሉግለሰቦች የወንጀል ሕጉ ካሳ አያስቀምጥም።

ሠ. ፍትሐዊ በሆነ ግልጽ ችሎት የመዳኘት መብትን መከልከል

ሕጉ ፍርድ ቤቶች ገለልተኛ መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል። የፍትሐ ብሔር ፍርድ ቤቶች በአብዛኛው በገለልተኝነት የሚሰሩ ቢሆኑም፣ የወንጀል ፍርድ ቤቶች ግን ደካማ እና በሥራ ጫና የተጨናነቁ ናቸው።

የፍርድ ሂደቶች

በሕገ መንግሥቱ መሠረት፣ ክስ የቀረበባቸው ሰዎች ካላስፈላጊ መዘግየት የፀዳ በግልጽ ችሎት እና በፍትሐዊ የፍርድ ሂደት ውሳኔ የማግኘት መብት ስላላቸው፣ ተከሳሾች ነጻ ተደርገው የመቆጠር መብት፣ በራሳቸው ምርጫ ጠበቃ የማቆም፣ ይግባኝ የመጠየቅ፣ በራሳቸው ላይ ያለመመስከር መብት፣ ምሥክሮች እና የመከላከያ ማስረጃ የማቅረብ እንዲሁም ለዓቃቤ ሕግ ምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ የማቅረብ መብት አላቸው። በሕጉ እንደሰፈረው ፣ ሰዎች በቁጥጥር ሥር የዋሉበትን ምክንያት ኃላፊዎች በግልጽ በተቀመጠ ጊዜ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው የሚደነግግ ሲሆን፤ የጊዜ ገደቡ እንደ ክሱ ክብደት ይለያያል። አስፈላጊ ከሆነ ተከሳሾች በሚረዱት ቋንቋ የፍርድ ሂደቱን እንዲከታተሉ አስተርጓሚ መመደብ እንዳለበት ሕጉ ይደነግጋል። የፌደራል ፍርድ ቤቶች ለዋና ዋና ቋንቋዎች አስተርጓሚዎች ነበሯቸው።ሌሎች ቋንቋዎችን ለሚናገሩ ተከሳሾች ደግሞ አስተርጓሚዎች እንዲቀጥሩ ሕጉ ያዛል።

በነሐሴ ወር የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የክልል ፍርድ ቤቶች የተከሳሾችን ነጻ ተደርጎ የመታየት መብት በሚገባ እንዳከበሩ ዘግቧል ። ኮሚሽኑፍርድ ቤቶች የታሳሪዎች ቤተሰቦች ስለእስሩ መረጃ ማግኘታቸውን ያረጋግጣሉ።

የፌደራል መንግሥት የተከላካይ ጠበቆች መሥሪያ ቤት አቅም ለሌላቸው ተከሳሾች የሕግ ምክር አገልግሎት የሰጠ ሲሆን፣ በጠበቆች እጥረት ምክንያት የአገልግሎቱ ስፋት እና ጥራት ግን በቂ አይደለም። አንድ በመንግሥት ተቀጥሮ ለተከሳሾች አገልግሎት የሚሰጥ ጠበቃ ከ100 በላይ ጉዳዮችን ከመያዙም በላይ ፣ ለተመሳሳይ የወንጀል ጉዳይ በርካታ ተከሳሾችን ሊወክል ይችላል። በዋናነት በዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ያሉ በርካታ ነጻ የሕግ አገልግሎት መስጫማዕከላት፣ የሕግ አገልግሎት ሰጥተዋል። በአንዳንድ የአገሪቱ አካባቢዎች በጎ ፈቃደኞች፣ ለምሳሌ የሕግ ተማሪዎች እና የሕግ መምህራን ያለክፍያ የሕግ አገልግሎት

እንዲሰጡ ሕጉ ይፈቅድላቸዋል። ጠንካራ የአገር ውስጥ የጠበቆች ማኅበር ወይም ሌላ ደረጃውን የጠበቀ የወንጀል መከላከያ ውክልና ደንብ ግን የለም።

በሕገ መንግሥቱ ኃይማኖታዊ እና ባሕላዊ የፍርድ ሥርዓቶች ዕውቅና ተሰጥቷቸዋል። በገጠር አካባቢ የሚኖሩ በርካታ ዜጎች ለመደበኛ የፍርድ ሥርዓቶች ያላቸው ተደራሽነት የተገደበ በመሆኑ፣ አለመግባባትን ለመፍታት በአብዛኛው የሚተማመኑት በባሕላዊ የፍርድ አካሄዶች ነው። በሕጉ እንደተቀመጠው ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸው በባሕላዊ ወይም በኃይማኖታዊ ፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በእነዚህ ተቋማት እንዲታይላቸው ቀድመው መስማማት ይጠበቅባቸዋል።የትኛውም ተከራካሪ ወገን ግን በማንኛውም ጊዜ በመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊጠይቅ ይችላል። የሸሪዓ (እስላማዊ) ፍርድ ቤቶች ኃይማኖታዊ እና የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች ያሉባቸውን የቤተሰብ ጉዳዮች ያያሉ፤ ይህም የሚሆነው ሁለቱም ተከራካሪ ወገኖች ይፋዊ የሕግ ሂደት መታየት ከመጀመሩ በፊት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኞች ከሆኑ ነው። የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ከመንግሥት የተወሰነ የገንዘብ ድጋፍ አግኝተዋል። እነዚህ የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች የእስልምና ተከታይ በሚበዛባቸው በሶማሌ እና አፋር ክልሎች በበርካታ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ሰጥተዋል። ሌሎች ባሕላዊ ሥርዓቶች፣ ለምሳሌ የአገር ሽማግሌዎች በተለይ በገጠር አካባቢዎች አገልግሎት ሰጥተዋል። ሴቶች ብዙውን ጊዜ በባሕላዊ የፍርድ አሰጣጥ ሥርዓቶች ነጻ እና ፍትሐዊ ዳኝነትእንዳልተሰጣቸው ይናገራሉ፤ ምክንያቱም የአካባቢው ባሕል በሽምግልና ጉባዔው እንዳይሳተፉ ስሚከለክላቸው እና አሁንም ድረስ ሊቀረፍ ያልቻለ የጾታ መድልዎ ያለ በመሆኑ ነው።

የፖለቲካ እስረኞች እና ታሳሪዎች

በወንጀል ድርጊት ምክንያት በገፍ ታስረው የተለቀቁ ወይም ቅጣት የተጣለባቸው የፖለቲካ መሪዎች ነበሩ። ሃጫሉ ሁንዴሳ በመገደሉ ምክንያት የሰኔ 23ቱን ረብሻ ተከትሎ በግምት 40 ያህል የፖለቲካ መሪዎች እና የእነርሱ ተከታዮች ታስረዋል። በሐምሌ ወር ዋና ዋናዎቹ የፖ ለትካ መሪዎች፣ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት እና በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ቢያንስ ለሦስት ጊዜያት ተጎብኝተዋል። እነዚህ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ሌሎች ታሳሪዎች የሚያገኙትን ዓይነት ጥበቃ ሲደረግላቸው ነበር። የሃጫሉ ሁንዴሳን ሞት ተከትሎ የታሰሩ አብዛኞቹ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች አሁንም የፍርድ ሂደታቸውን በመጠባበቅ በእስር ላይ ናቸው።

የፍትሐ ብሔር ስርዓቶች እና መፍትሔዎች

ዜጎች አቤቱታቸውን ለፍትሐ ብሔር ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት ያላቸው ሲሆን፣ አቤቱታ ሊያቀርቡባቸው የሚችሏቸው ጉዳዮች የሰብዓዊ መብት ጥሰትን እንደሚጨምሩ ይደነግጋል። የሰብዓዊ መብትን ጥሷል የተባለው አካል የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚሆንበት ጊዜ፣ ተጠቂው ሰው አቤቱታዉን መጀመሪያ ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ያቀርባል። የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽኑ ጉዳዮችን ከመረመረ በኋላ ለሚመለከተው የመንግሥት ኤጀንሲ ምክረ ሀሳብያቀርባል።

ረ. በግል ሕይወት፣ በቤቴሰብ፣ በመኖሪያ ቤት ወይም በደብዳቤ ልውውጥ ላይ በዘፈቀደ ወይም ከህግ ውጭ የሆነ ጣልቃ ገብነት

በግል ንብረት ላይ ፍተሻ ከማካሔድ አስቀድሞ ባለስልጣናት የፍርድ ቤት ማዘዣ ማግኘት እንዳለባቸው ሕጉ ይደነግጋል። በአፋጣኝ የክትትል ወቅት ተጠርጣሪ ው ቅጥር ግቢዎች ውስጥ ዘሎ ቢገባ ወይም ጥፋት የተፈጸመባቸውን ቁሳቁሶች ለመሰወር ቢሞክርህጉ ለየት ላሉ ሁኔታዎች እውቅና ይሰጣል። በዚህ ለየት ላለ ሁኔታ የፖሊስ አባላት በዚያ ቅጥር ግቢ ውስጥ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ከሦስት ዓመት በላይ የእስር ቅጣት ሊያስከትል የሚችል ወንጀል ማስረጃ በዚያ ግቢ ውስጥ ተደብቋል የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖራቸው ወይም የፍተሻ ትዕዛዝ ከፍርድ ቤት ማግኘት ጊዜ ስለሚፈጅ መረጃው ሊወገድ ይችላል ብለው ካመኑ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ፍተሻ ማድረግ ይችላሉ።

<u>ሰ. በውስጣዊ ግጭት ምክንያት የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶች</u>

መንግሥት ተ ገንጣይ ታጣቂ በሆነው ኦነግ-ሸኔ ላይ በምዕራብ፣ በሰሜን እና በደቡብ ኦሮሚያ አካባቢዎች የማጥቃት ኦፕሬሽን አካሄደ። መንግሥት ሁሉንም የጸጥታ ኦፕሬሽኖች የሚያስተባብሩ በወታደር የሚመሩ ኮማንድ ፖስቶች በእነዚህ አካባቢዎች ነበሩት። ኮማንድ ፖስቶች የሚመሩት በኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ሰራዊት ቢሆንም ፣ በክልል ልዩ ኃይሎች፣ በክልል ፖሊስ እና በክልል ሚሊሻ እገዛ ይደረግላቸዋል።

ጥቅምት 25 ቀን በኢትዮጵያ አገር መከላከያ ሰራዊት እና በትግራይ ልዩ ኃይል መካከል ጦርነት ተጀምሮ በሰሜን ትግራይ የተራዘመ ግጭትን አስከተለ። ጦርነቱም በመላው ክልል ላይ ተጽዕኖ አደረሰ። ከዓመቱ መጨረሻ ጀምሮ፣ ከመቀሌ በስተቀር ሌላው የክልሉ ክፍል ያለው ተደራሽነት እጅግ በመገደቡ ሪፖርት እንዳይኖር እና በመብት ላይ የተፈጸሙ ጥሰቶች እንዳይረጋገጡ ችግር አስከተለ። በትግራይ የ ስደተኛ ካምፖችን ጨምሮበርካታ ዝርፍያዎች እና የመሠረተ ልማት ውድመቶችስለመድረሳቸው ሪፖርቶች ቀርበዋል። የመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች፣ የአጎራባች ክልሎች የጸጥታ ኃይሎች፣ የኤርትራ ሰራዊት ፣ ግለሰብሚሊሻዎች እና የሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ የክልል የጸጥታ ኃይሎች ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰዎችን መግደል፣ ወሲባዊ ጥቃቶችን መፈጸም፣ ሲቪል ነዋሪዎችን በግዳጅ ማፈናቀል እና ስቃይ የመሰሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን መፈጸማቸው ይነገራል ። በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በዘፈቀደ በቁጥጥር ስር ማዋል እና እስር እንደሚፈጸም ሪፖርቶች ይቀርባሉ። ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች፣ የተባበሩት መንግሥታትን ጨምሮ፣ በትግራይ ውስጥ ሰብዓዊ ቀውስ በመከተሉ፣ የመሠረታዊ አገልግሎቶችአቅርቦት፣ የምግብ እና የሕክምና አቅርቦቶችን እገዛ ለማድረግ መዘጋጀታቸውንገልጸዋል።

<u>ግድያዎች</u>፡- በኦሮሚያ ቄለም ወለጋ ዞን ነዋሪዎች ለመገናኛ ብዙሃን እንደገለጹት፣ የመንግሥት ጸጥታ ኃይሎች ሰባት ሲቪሎችን ገድለዋል።

የኦሮሚያ ክልል የደህንነት መሥሪያ ቤት ሪፖርት እንዳመለከተው የኦነግ ሸኔ ተዋጊዎች ከ770 በላይ ግለሰቦችን ገድለው፣ ከ1300 በላይ አቁስለው 72 ሰዎችን አፍነው ወስደዋል።

ጥቅምት 22 ቀን ተጠርጣሪ የኦነግ ሸኔ ተዋጊዎች በምዕራብ ወለጋ ዞን፣ በጋዋ ቃንቃ ቢያንስ 54 የአማራ ብሔር ተወላጆችን መግደላቸውን አምነስቲ ኢንተርናሽናል አሳውቋል። ምሥክሮች እንዳሉት ወንዶች፣ ሴቶች እና ህፃናትተገድለዋል፣ ንብረቶች ተዘርፈዋል፣ ተቃጥለዋል።

ክፍል 2. የሚከተሉትን ጨምሮ፣ ሌሎች የሲቪል መብቶችን ማክበር

ሀ. ፕሬስን ጨምሮ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት፣

ሕገ መንግሥቱ እና ሕጉ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት እና የፕሬስ ነጻነት እንዲከበር የሚደነግጉ ሲሆን፣በኣጠቃላይ መንግሥት ይህን መብትያከብራል›። መንግሥት በጠቅላላው የፖለቲካ ምህዳሩን ከፍቷል። ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን ጨምሮ። ይህም ለአዳዲስ የመገናኛ ብዙሃን መበራከትእና አንዳንድ የዳያስፖራው መገናኛ ብዙሃንም ወደ ሀገር ቤት እንዲመለሱ አድርጓል።

መጋቢት 14 ቀን መንግሥት የጥላቻ ንግግርን እና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን መከላከያ እና መቆጣጠሪያ አዋጅቁጥር 1185/2020ን አጸደቀ። የአገር ውስጥ የሰብዓዊ መብት ቡድኖች ይህ ሕግ ሰፊ የህግ ትርጓሜ በመያዝ ሃሳብን የመግለጽ መብትን ለማፈን መጠቀሚያ ሊሆን ይችላል የሚል ትችት አቅርበዋል ።መንግሥት ይህንን ሕግ ለአንዳንድ ሁኔታዎች ተግባራዊ አድርጓል (ክፍል 2.ሀ. ን የሲቪል ነጻነቶችን ስማክበር፣ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት-- የበይነ መረብ ነጻነት የሚለውን ክፍል ይመልከቱ) ።

<u>ሃሳብን የመግለጽ ነጻነት</u>፡- ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኃላ፣ የመናገር ነፃነት ለአገሪቱ የወደፊት ዕጣ ፈንታ አስፈላጊ እንደሆነ ተናግረዋል ። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይህንን ተከትለው እንደገለጹት መንግሥት ላይ ሂስ የሚያቀርቡ ሰዎችን በቁጥጥር ስር ማዋል፣ ማሰር፣ ጥቃት የማድረስ ልምዶች ጉልህ በሆነ ደረጃ ቀንሰዋል።

መጋቢት 26 ቀን ኤልሳቤጥ ከበደ በኮቪድ-19 የተያዙ ሰዎችን ስሞች እና ብሔራቸውንበመጻፏበአዲስ አበባ ፖሊስ በቁጥጥር ስር ውላ ነበር። ለአንድ ወር በእስር ከቆየች በኋላ ሚያዝያ 30 ቀን ክስ ሳይመሰረትባት በዋስ ተለቃለች።

<u>የበይነ መረብን ጨምሮ፣ የፕሬስ እና የሚዲያ ነጻነት</u>፡- ገለልተኛ ሚዲያዎች በንቃት እና ያለገደብ ልዩ ልዩ ሃሳቦችን አቅርበዋል።

በአብይ አስተዳደር የዜና አውታሮች ቁጥር ጨምሯል። በጥር 2011 እና በጥቅምት 2012 መካከል የሕትመት ሚዲያው ጋዜጦች ቁጥር ከስድስት ወደ ስምንት አድጓል። ጋዜጦቹ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚታተሙ ናቸው። በአንድ ወቅት ጥቂት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የነበሩ የቴሌቪዥን ጣቢያዎችወደ 31 አድገዋል፤ አብዛኞቹ የግል ጣቢያዎች ናቸው። እነዚህ ጣቢያዎች ብሔራዊ እና ክልላዊ ጥቅሞችን ይወክላሉ።

ብሔራዊ፣ አዲስ አበባ እና ክልላዊ ሽፋን ያላቸው የሬዲዮ ጣቢያዎች በግምት ከ10 ወደ 14 አድገዋል። የማኅበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያዎችም እንዲሁ በስፋት ተሰራጭተዋል።

በማደግ ላይ ያለው የመገናኛ ብዙሃን ምህዳር ተግዳሮቶችን አስከትሏል ። የሚዲያው አውድ በከፍተኛ ደረጃ መስፋፋት፣ የሚዲያ ተቆማትሥልጠና ያላገኙ ሪፖርተሮች እንዲኖሯቸው አደረገ። በርከት ያሉ አዲስ የግል የዜና ተቆማትየባለቤቶቻቸውን አመለካከቶች ነው የሚያንጸባርቁት። ማህበራዊ የሚዲያ ተፅዕኖ አድራጊዎችን ጨምሮ የክልል የዜና ማሰራጫዎች መበራከት፣ ለብሔር ፍላጎቶች ያደሉ መልዕክቶች ጎልተው እንዲወጡ አድርጎል።

<u>ሁከት እና ትንኮሳ</u> ፡- ኦሮሞ ዘፋኝ እና አክቲቪስት የነበረው ሃጫሉ ሁንዴሳ ከተገደለ በኋላ በሰኔ 23 እና በሰኔ 29 መካከል መንግሥት በግምት 12 ጋዜጠኞች እና የካሜራ ባለሙያዎችን በቁጥጥር ስር አውሏል። ሐምሌ 23 ቀን ፖሊስ ከአንድ የፖለቲካ መሪ መኖሪያ ቤት ውጪ ያሲን ጁማ የተባለውን ኬኒያዊ ጋዜጠኛ አስሯል። ጁማ በተደጋጋሚ በፍርድ ቤት ከቀረበ እና የክሱ ሂደት ከተጓተተ በኋላ ነሐሴ 14 ቀን በዋስ ተለቋል።

ጥቅምት 25 ቀን በአዲስ አበባ ውስጥ ፖሊስ የአውሎ ሚዲያውን ጋዜጠኛ በቃሉ አላምረውን አስሯል፤ የቀረበበትም ክስ የሀሰት ዘገባ አስተላልፈሃል፣ የመንግሥትን ስም አጥፍተሃል እንዲሁም በብሔሮች መካከል ውጥረት እንዲፈጠር አነሳስተሃል የሚል ነው። በቃሉ አላምረው በምዕራብ ወለጋ ስለተገደሉ የአማራ ተወላጆች ዘግቦ ነበር። በኅዳር 14 ቀን ፖሊስ በፍርድ ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት በቃሉ አላምረውን ከእስር ፈቷል። ጥቅምት 28 ቀን *አዲስ ስታንዳርድ* የተባለው የዜና ድረ ገጽ አርታኢየሆነውን መድሃኔ እቁበሚካኤል አስሮ በኋላም "ሕገ መንግሥቱን በኃይል ለማፍረስ መሞከር" የሚል ክስ መስርቶበታል። መድሃኔ እቁባሚካኤል በድረ ገጹ ላይ በትግራይ ስላለው ግጭት የሚቀርበውን ዘገባ ይመራ ነበር።

ሐምሌ 9 ቀን ፌደራል ፖሊስ ጉዮ ዋሪዮ የተባለ የኦሮሚያ ሚዲያ ኔትወርክ ጋዜጠኛ አሰረ። ተከሳሹ በተደጋጋሚ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ዓቃቤ ሕግ በቂ ማስረጃ አላቀረበም በማለት ፍርድ ቤቱ ነሐሴ 26 ቀን ጉዮ ዋሪዮን ከእስር ለቋል። በሐምሌ ወር አራት ተጨማሪ የኦሮሚያ ሚዲያ ኔትወርክ ጋዜጠኞች በቁጥጥር ሥር ውለዋል። በዓመቱ መጨረሻ ከመካከላቸውአንድ ጋዜጠኛ በእስር ላይ ነበር። ሐምሌ 29 ፖሊስ የአስራት ሚዲያ አባላት

የሆኑ ሁለት ጋዜጠኞችን እና ሁለት የካሜራ ባለሙያዎችን አሰረ፤ የቀረበባቸው ክስም ለዓመጽ ማነሳሳት የሚል ነው። ፍርድ ቤት ጳጉሜ 2 ቀን የዋስ መብታቸውን ቢያከብርላቸውም ፣ ፖሊስ በቀጣዩ ቀን በቁጥጥር ስር አውሏቸዋል። መስከረም 9 ቀን ፖሊስ በፍርድ ቤት በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የአስራት ሚዲያ ጋዜጠኞችን ከእስር ፈትቷል።

<u>ብሔራዊ ደህንነት</u>፡- መንግሥት አንዳንድ ጋዜጠኞችን ከብሔራዊ ደህንነት ጋር በተያያዘ አስሯል። መጋቢት 17 ቀን መንግሥት ከኮቪድ-19 ጋር በተያያዘ የጅምላ ቀብር ስፍራዎች ተዘጋጅቷል የሚል ዘገባ በመስራቱ ምክንያት ጋዜጠኛ ያየሰው ሺመልስን በቁጥጥር ስር አዋለ። ሚያዝያ 15 ቀን ፍርድ ቤት በዋስ እንዲፈታ ትዕዛዝ ሰጠ። በመጀመሪያ በጋዜጠኛው ላይ የሽብር ክስ ቀርቦ የነበረ ሲሆን፤ ክሱ የጥላቻ ንግግር እና የሐሰት መረጃ መከላከል እና ቁጥጥር አዋጅን ጥሰሃል ወደሚል ተቀየረ። በዚህ ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ሳይሰጥ በዋስ ተፈትቷል።

<u>መንግሥታዊ ያልሆነ ተጽዕኖ</u>፡- ኦነግ-ሸኔ ጋዜጠኞች ሊገቡበት የማይችሉ ስፍራዎችን ይቆጣጠራል። በዚህ ዓመት ውስጥ ጥቂት ጋዜጠኞች ብቻ ወደ አካባቢው ሊገቡ ቢችሉም፣ ተጠሪነታቸው ለክልል ፕሬዚደንት በሆኑ የክልል የጸጥታ ኃይሎች ታስረዋል።

ጥር 5 ቀን ፖሊስ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ አሶሳ ለትግራይ ቲቪ የአማርኛ ክፍል የሚሰራን አንድ ጋዜጠኛ እና የካሜራ ሙያተኛ በቁጥጥር ስር አዋለ። ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ እና የካሜራ ባለሙያው በሃይሉ ውቤ ወደ አሶሳ የተጓዙት የፖለቲካ ፓርቲዎችን መድረክ ሽፋን ለመስጠት ሲሆን፣ እንደ ትግራይ ቲቪ ኃላፊዎች፣ ዳዊት ከበደ ወደ ሥፍራው የሄደው በመድረኩ አዘጋጆች ግብዣ መሰረት ነበር።የቤኒሻንጉል ክልል የኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ እንዳሉት፣ ጋዜጠኞቹ ወደ ክልሉ ሲጓዙ ለክልሉ የኮሙኒኬሽን ቢሮ ባለማሳወቃቸው አሰራር ጥሰዋል ብለዋል። ሁለቱም ከሁለት ቀናት በኋላ ተፈቱ።

የኢንተርኔት ነጻነት

መንግስት በየጊዜው ኢንተርኔትን ሲገድብ እና ሲያቋርጥ ቆይቷል። የማኅበራዊ ሚዲያ ድረ ገጾችም የተዘጉባቸው ወቅቶች ነበሩ። ከጥር እስከ መጋቢት መንግሥት በኦሮሚያ ክልል

በወለጋ እና ጉጂ ዞኖች ሙሉ ለሙሉ ኢንተርኔትን አቋርጦ ቆይቷል። በዓመቱ መጨረሻም በኦሮሚያ ጉጂ ዞን በየወቅቱ የኢንተርኔት አገልግሎት ሲቋረጥ ነበር።

ከሰኔ 23 ቀን አስከ ሐምሌ 16፣ የሃጫሉ ሁንዴሳን መገደል ተከትሎ በኦሮሚያ እና በአዲስ አበባ ረብሻ በመከሰቱ መንግሥት በመላው አገሪቱ ኢንተርኔት ዘግቷል። ሐምሌ 8 በአዲስ አበባ የኢንተርኔት አገልግሎት በከፊል የተመለሰ ሲሆን፣በሐምሌ 16 በመላ ሀገሪቱ የኢንተርኔት አገልግሎት ተመልሷል።

ጥቅምት 25 ቀን በትግራይ ክልል የመስመር ስልክ፣ የእጅ ስልክ እና የኢንተርኔት አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ተቋርጠውየነበረ ሲሆን፣ ታኅሳስ 22 ቀን ኢንተርኔቱን ሳይጨምርየስልክ አገልግሎት በክልሉመሻሻል አሳይቷል።

የጥላቻ ንግግር እና የሃሰት መረጃ መከላከል እና ቁጥጥር አዋጅ በማኅበራዊ ሚዲያው የሚሰራጭ የጥላቻ ንግግርን ይመለከታል። ሕጉ የጽሑፍ መልዕክትን፣ ምስልን፣ ድምጽን እና ቪድዮን በመጠቀም የጥላቻ ንግግርን እና የሃሰት መረጃዎችን በብሮድካስት፣ በሕትመት ወይም በማኅበራዊ ሚዲያ ማሰራጨትን ይከለክላል። በዚህ ሕግ ሥር በተጠቀሰው ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘት ከሁለት ዓመት ያልበለጠ እስር ወይምከፍተኛ የገንዘብ ቅጣትን ያስከትላል። የሀሰት መረጃ ህግን የሚጥስ ሰው ከአንድ ዓመት የማይበልጥ እስር ወይምከፍተኛ የገንዘብ ቅጣት ሊበየንበት ይችላል። በእነርሱ የጥላቻ ንግግር ምክንያት በአንድ ሰው ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የደረሰ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ እስር ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው የጥላቻ ንግግር ወይም የሃሰት መረጃ በብሮድካስቲንግ አገልግሎት፣ በሕትመት ሚዲያ ወይም ከ5000 በላይ ተከታዮች ባሉት ማኅበራዊ ሚዲያ አማካኝነት በማሰራጨት ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ፣ ከአንድ እስከ ሦስት ዓመታት የሚደርስ እስራት ወይም ከፍተኛ መጠን ያለው የገንዘብ ቅጣት ይወሰንበታል። በዓመቱ መጨረሻ በዚህ አንቀጽ አንድ በሂደት ላይ ያለ ጉዳይ ነበረ።

አካዳሚያዊ ነጻነት እና ባሕላዊ ክስተቶች

በዓመቱ ውስጥ መንግሥት የትምህርት ሥርዓቱ በይበልጥ ብቃት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን እና የአዳሚክ ነጻነትን በሚያጎናጽፍ መልኩ ማሻሻያ አድርጓል ። በዚህም መሠረት

የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን በትምህርታዊ ብቃት ላይ በተመሠረተ ሥርዓት እንጂ ከፖርቲ ጋር ባላቸው ቅርበት እንዳይመደቡ ሆኗል። ፍሪደም ሃውስ የተባለው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ፖለቲካዊ ኢንዶክትሪኔሽን እንዲሰጣቸው እና ፖርቲውን እንዲቀላቀሉ ይደረግ የነበረው ጫና መቀነሱን ተገንዝቧል።

ሥርዓተ ትምህርትን በሚመለከት ተፈጻሚነት ያላቸው ሕግጋት አሁንም እ.ኤ.አ. በ2009 በወጣው ሕግ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ይህ አዋጅ ከዓለም አቀፍ መልካም ልምምዶች እና ከባህላዊ ሃላፊነቶች ጋር የሚጣጣሙ ዝቅተኛ በሆኑ መስፈርቶች የአካዳሚክ ነፃነትን ይገድባል ።

ለ. የሰላማዊ ስብሰባ እና የመደራጀት ነፃነት

ሕገ መንግሥቱ እና ሕ ጉ ሰላማዊ ስብሰባን እና የመደራጀት መብትን የሚፈቅዱ ሲሆን፤ መንግሥት**ም** በአጠቃላይ እነዚህን መብቶች አክብሯል።

በሰላማዊ መንገድ የመሰብሰብ ነፃነት

አርምድ ኮንፍሊክት ኤንድ ኢቨንት ዳታቤዝ የተባለ በመያድ የሚመራ ተቋም በአገሪቱ በየሳምንቱ ሰላማዊ ሰልፍ ይካሄድ እንደነበር ዘግቧል። አብዛኞቹ እነዚህ ሰልፎች ሰላማዊ የነበሩ ቢሆንም፣ በኦሮሚያ ውስጥ ከፍተኛ ህዝባዊ አመፅ ከቀሰቀሰው ከሃጫሉ ሁንዴሳ ግደያ በኋላ የተካሄዱት ሰልፎች ግን ሰላማዊ አልነበሩም ።

መጋቢት 30 እና ነሐሴ 30 በነበረው ግዜየመንግሥት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የኮቪድ-19ን ስርጭት ለመከላከል በርካታ ሰዎች በአንድነት እንዳይሰበሰቡ ከለከለ። ይህም ግለሰቦች በአምልኮ ስፍራዎች እና በሥልጠና መስጫዎች እንዳይሰባሰቡ አድርጓል። እንዲሁም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ተፈጻሚ ከሆነ በኋላአዋጁን ጥሳችኋል በሚል ቢያንስ 1,600 ዜጎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ሆኗል። የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እነዚህ በቁጥጥር ሥር የማዋል ተግባራትን ሕገወጥ እና የዘፈቀደ በመሆናቸው በአፋጣኝ መቆም አለባቸው የሚል መግለጫ እንዲያወጣባቸው አድርጓል። ፖሊስ ከታሰሩት ውስጥ አብዛኞቹን ከተያዙ በኋላ በ 48 ሰዓታት ውስጥ ለቀቀ።

ሐ. የሐይማኖት ነፃነት

በ https://www.state.gov/religiousfreedomreport/ላይ *የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤትን የዓለም አቀፍ ሐይማኖቶች ነጻነት ሪፖርትን* ይመልከቱ።

መ. የመንቀሳቀስ ነፃነት

ህጉ ለሀገር ውስጥ ዝውውር፣ ለውጭ ሐገር ጉዞ፣ ለውጭ ፍልሰት፣ እና ከውጭ ለመመለስ የመቻልን ነፃነት ይደነግጋል። መንግስት በአጠቃላይ እነዚህን መብቶች አክብሯል።

<u>የሐገር ውስጥ እንቅስቃሴ/ዝውውር፡-</u> የኮቪድ-19 የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ክልላዊ እንቅስቃሴ ላይ ገደብ ጥሏል። የክልል መንግሥታት በክልል ደንበሮች መካከል በሚደረጉ የዕቃዎች ዝውውርም ሆነ የሰዎች እንቅስቃሴዎች ላይ ልዩ ልዩ ገደቦች ጥለዋል። ጥብቅ የሆኑት የመከላከያ ገደቦች የተጣሉት በትግራይ ክልል ውስጥ ነበር። በሚያዚያ ወር በመላው የትግራይ ክልል ውስጥ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ተገድበው ነበር። ሌሎቹ ዘጠኝ ክልሎች ተመሳሳይ መመሪያዎች ነበሯቸው። እነርሱም ከክልል ወደ ክልል በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ገደቦች ሲጥሉ፣ በሕዝብ ማመላለሻ ውስጥ ሊሳፈሩ በሚችሉ ተሳፋሪዎች ብዛት ላይ ገደብ አስቀምጠዋል። የአማራ ክልልዊ መንግሥት ደግሞ በባህር ዳር፣ በቲሊሊ፣ እና በአዲስ ኪዳንም ተጨማሪ ገደቦች ያስቀመጠ ሲሆን፣ እነዚህ ከተሞች በሚያዚያ ውስጥ ሙሉ በሙሉ በክልሉ የጸጥታ ኃይል አማካኝነት በእንቅስቃሴ እቀባ ላይ ነበሩ። እነዚህ እርምጃዎች ሁሉ የተሻሩት ከነሐሴ 30 ቀን በፊት የኮቪድ 19 የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከማብቃቱ አስቀድሞ ነበር።

<u>ሠ. የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮችሁኔታ እና አያያዝ</u>

ጳጉሜን 5፣ ዓለም አቀፉ የፍልሰተኞች ተቋም (አይ ኦ ኤም) በአገሪቱ ከ1.8 ሚሊዮን በላይ በአገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች እንዳሉ በሪፖርቱ አመልክቷል ። የዚህ ሪፖርት መነሻአይ ኦ ኤምከሰኔ እስከ ሐምሌ ባለው ጊዜ ውስጥ በተወሰኑ ቦታዎች እና መንደሮች ያካሄዳቸው ግምገማዎች ነበሩ። እንደ አይ ኦ ኤም እምነትለመፈናቀል ዋነኛው ምክንያት ግጭት መሆኑናይህም በመላው አገሪቱ 1,233,557 ሰዎች እንዲፈናቀሉ ማድረጉን ገልጿል። ቀጣዩ

ዋነኛ ምክንያት ደግሞ ድርቅ ሲሆን ይህም ተጨማሪ 351,062 ሰዎች እንዲፈናቀሉ አድርጓል፤ ከዚያም ወቅት ጠብቆ የሚከሰት ጎርፍ (104,696) እና ድንገተኛ ጎርፍ (50,093 የአገር ውስጥ ተፈናቃዮች) እንዲፈናቀሉ ምክንያት ሆነዋል። የድምጻዊ ሃጫሉ ሁንዴሳን መገደል ተከትሎ ተጨማሪ 12,000 ሰዎች በመፈናቀላቸው ሁኔታውን ይበልጥ አባብሶታል።

ዓለም አቀፉ የፍልሰተኞች ተቋም እንዳመለከተው የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ለመሠረታዊ አገልግሎቶች እና የገቢ ማስገኛ ዕድሎች ያላቸው ተደራሽነት በጣም ውሱን ነበር። ከጥበቃ ጋር በተያያዘም ስጋት ላይ ነበሩ።፤ ቀጣይነት ላለው የሃይል ጥቃትተጋላጭ ከመሆናቸውም በላይ የትምህርት እና የጤና እንክብካቤ ዕድሎች የሉም። ተፈናቃዮች ከሚገኙባቸው ስፍራዎች መካከል 90 በመቶ የሚሆኑት የምግብ እጥረት ያለባቸው ሲሆኑ፣ በኮቪድ-19 ምክንያት የተቀመጡት ገደቦች በዋና ዋና አቅርቦቶች ላይ ዕጥረቶች እንዲኖሩ አድርገዋል። በአንዳንድ አጋጣሚዎች መንግሥት ለደህንነት እና ቀጣይነት ላለው ኑሮ ሁኔታዎችን ሳያመቻች ተፈናቃዮች ወደ መኖሪያ ስፍራቸው እንዲመለሱ በእጅጉ ያበረታታል።

በታኅሳስ 2012 አገሪቱ እና የተባበሩት መንግሥታት በመላው አገሪቱ ቀጣይነት ያላቸውን የመፍትሔዎች አቅጣጫን ነደፉ፤ ዓላማውም ለአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ደህንነታቸውን የሚያረጋግጡ፣ ክብራቸውን የሚጠብቁ እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ ዘላቂ መፍትሔዎችን መሻት ነው።

<u>ረ. ለስደተኞች የሚደረግ ጥበቃ</u>

መንግሥት ከተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) እና ከሌሎች ሰብዓዊ ድጋፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለአገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ ለስደተኞች ለተመላሽ ስደተኞች፣ ለፖለቲካ ጥገኝነት ጠያቂዎች፣ ለአገር አልባ ሰዎች እና ለሌሎች አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ለሚገኙ ሰዎች ጥበቃ ለማድረግ እና ሌሎች ድጋፎችን ለመስጠት ሰርቷል። በትግራይ ውስጥ ጦርነት በሚካሄድባቸው ጊዜያት የኤርትራ ስደተኞች በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ሆነዋል። በሽመልባ፣ በህጻጽ፣ በማይ-አይኒ እና በአዲ ሃሩሽ ካምፖች በግምት 96,000 ያህል ስደተኞች ይኖራሉ። ሕጻጽ እና ሽመልባ በኤርትራ-ኢትዮጵያ ድንበር አቅራቢያ የሚገኙ ካምፖች ናቸው። በኢትዮጵያ የአገር መከላከያ ኃይል እና በሕዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ የክልል የጸጥታ ኃይሎች መካከል ያለው ጦርነት የሚካሄደውበዚህ አቅራቢያ ነበር ። ግጭቱ

ወደ ጎዳር ማብቂያ እና ታኅሳስ ወር መግቢያ በመቀጠሉ እና መዳረሻው በማስቸገሩ በካምፖቹ ውስጥ ያለው አሳሳቢ ሁኔታ ይበልጥ ተባብሶ፤ ስደተኞች ምግብ፣ ውሃ እና የሕክምና ቁሳቁሶችየማግኘት እድላቸው ዕጅግ የተገደበ ሆነ። እንዲሁም ግጭቱን በመፍራት ስደተኛ ካምፑን ትተው ሄደው የነበሩ ስደተኞች ወደ ስደተኛ ካምፑ በመንግስት ተገደው እንዲመለሱ እንደሚደረግ ሪፖርት ቀርቧል። ወደ ኤርትራ በግዳጅ የመመለስ ሁኔታዎች እንደነበሩ ሪፖርቶች አመልክተዋል። በትግራይ በሚገኙ ስደተኞች ላይ የሃይል ጥቃት እንደሚፈጸም ሪፖርቶች አመልክተዋል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ታኅሳስ 19 እንደገለጸው፣ እህል የጫኑ ተሽከርካሪዎች ወደ አዲ ሃሩሽ እና ማይ ዓይኒ የስደተኞች ካምፖች በመግባት በግምት 490 ሜትሪክ ቶን ምግብ አሰራጭተዋል።

<u>ጥገኝነት የማግኘት እድል፡-</u> ህጉ የጥገኝነት ወይም የስደተኝነት ደረጃ ለመስጠት የደነገገ ሲሆን፣ መንግስት ለስደተኞች አገልግሎት እና ጥበቃ ለመስጠት በየስደተኝነት ደረጃ መወሰኛ ስርዓት ተጠቅሟል። በጥር ወር የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ኤጀንሲ ኤርትራዊያንን በሚመዘግብበት አሰራር ላይ ለውጥ እንደሚያደርግ አሳወቀ። ለኤርትራዊያን ህጋዊ እና ተቀባይነት ያለው ሆኖ ስደተኝነትን የሚያሟላ ሁኔታ በመፍቀድ ፈንታ የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ኤጀንሲ ለአዲስ መጦች የተናጠል የስደተኛ ሁኔታ መግለጫ ሥርዓትን ተግባራዊ አድርጓል።። ይህ መግለጫ ከተነገረ በኋላ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) ሪፖርት እንዳደረገው የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ኤጀንሲ በዋናነት የመዘገበው፣ በግዳጅ ወደ ውትድርና እንዲገቡ እና የፖለቲካ ስደት እንደደረሰባቸው የተናገሩ ኤርትራዊያንን ብቻ ነበር ። የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን ሊከሰት የሚችለውን አገልግሎት አለማግኘት እና የጥገኝነት ጥያቄ ውድቅ መደረግ በተለይ ደግሞ ከአዋቂ ጋር ያልሆኑ ሕጻናትን፣ ከቤተሰብ ጋር መቀላቀል የሚፈልጉ ስደተኞችን እና የሕክምና እርዳታ የሚሹትን አስመልክቶ ጉዳዩ እንደሚያሳስበው አንስቷል።

<u>የመንቀሳቀስ ነጻነት</u>፡- ግንቦት 30 የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ኤጀንሲ ስደተኞች አንዳንድ መስፈርቶችን ካሟሉ ካምፖቹን ለቅቀው መወጣት እንደሚችሉ የሚደነግግ መመሪያ አወጣ።

የሥራ ቅጥር፡- ግንቦት 30 የስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች ኤጀንሲ፣ በ2012 የወጣውን የስደተኞች አዋጅ ለማስፈጸም፣ ሁለተኛ ደረጃ ያለው ሕግ አወጣ። ይህም ስደኞች ሥራ የመስራት መብት እንዳላቸው ይደነግጋል። በዚህ መመሪያ መሠረት ስደተኞች ከኢትዮጵያዊያን ዜጎች ጋር በጋራ ፕሮጀክቶች ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም በኢትዮጵያዊያን ሊሸፈኑ በማይችሉ የሥራ መደቦች ላይ ተቀጥረው መሥራት እንዲችሉም አለበለዚያም በራሳቸው ሥራ ላይ መሰማራት እንደሚችሉም ተደንግጓል።

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት፡- አስፈላጊ ፈተናዎችን ያለፉ ስደተኛ ተማሪዎች በመንግሥት እና በተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን በሚፈፀም ክፍያ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት መከታተል ይችላሉ።

ዘላቂ መፍትሔዎች፡- መንግስት ስደተኞችን በሐገሪቱ ውስጥ እንዲኖሩ የሚያስተናግድ ቢሆንም፣ ዜግነት ሊያገኙ የሚችሉበትን መንገድ አልገለጸም ወይም ውህደት እንዲፈጽሙ አላደረገም።

ክፍል 3፡ በፖለቲካ ሂደት የመሳተፍ ነፃነት

ህገ-መንግስቱ እና ህጉ ዜጎች በሚስጥር ድምጽ በሚሰጡ እና ሁሉን አቀፍ እና በእኩል ምርጫ ላይ በተመሰረቱ ነፃ እና ፍትሃዊ ወቅታዊ ምርጫዎች መንግስታቸውን የመምረጥ አቅም/መብት ይሰጣቸዋል ።

ምርጫዎችና ፖለቲካዊ ተሳትፎ

የቅርብ ጊዜ ምርጫዎች፡- አገሪቱ በ2007 ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ብሔራዊ ምርጫ አካሂዳለች። በዚያ ዓመት ፓርላማው አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝን ሲሾም እርሳቸውም ለመጀሪያ ጊዜ ሙሉ የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ሥልጣን አገኙ። በ2010 ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ ከሥልጣናቸው በገዛ ፈቃዳቸው እንደሚለቁ ሲያስታውቁ ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር ዐቢይ አሕመድን አዲሱ የኢሕአዴግ ሊቀመንበር አድርጎ ፣ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት እጩ እንዲሆኑ መረጣቸው። በምክር ቤቱ ባገኙት የድጋፍ ድምጽም ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ።

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ እና ተያያዥ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በግንቦት ወር እንዲካሄድ ታቅዶ የነበረውን ምርጫ እንዲዘገይ አደረጉ። ፓርላማው ምርጫው እንዲራዘም ያደረገው ወረርሺኙን ለመከላከል የተወሰዱ እርምጃዎች መሰብሰብ በሚችሉ ሰዎች ቁጥር ላይ ገደብ ከማስቀመጡም ባሻገር ፣ ሕዝባዊ መሰብሰብያዎች መዘጋት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለምርጫው ለመዘጋጀት ሥልጠና የመስጠትን አቅም የሚገደብ በመሆኑ ነው። መስከረም 12 ቀን ፓርላማው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እስከ መስከረም 2014 አገር አቀፍ ምርጫ እንዲያዘጋጅ ፈቃድ ሰጠ።

<u>የፖለቲካ ፓርቲዎችና ፖለቲካዊ ተሳትፎ፡-</u> መንግስት በትጥቅ ትግል ላይ ያሉትን ጨምሮ ተቀማጭነታቸው በውጭ ሐገር የሆነ ተቃዋሚ ቡድኖች ተመልሰው ከነውጥ የጸዳ ትግል እንዲያካሂዱ ፈቀደ። በታኅሳስ ወር 78 የተመዘገቡ ፓርቲዎች በፓርላማው ምርጫ ላይ እንዲሳተፉ ፈቃድ አግኝተዋል።

የተመዘገቡ የፖለቲከ ፓርቲዎች ቢሮዎችን በየአካባቢው ለመክፈት ከክልል መንግስታት ፈቃድ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ሕጉ ፓርቲዎች "ህዝባዊ ስብሰባዎችን" ሪፖርት እንዲያደርጉና ለህዝብ የድጋፍ ሰልፎች ፈቃድ ማግኘት እንዳለባቸው ይደነግጋል።

<u>የሴቶችና የአናሳ ቡድኖች አባላት ተሳትፎ፡-</u>በአንዳንድ ክልሎች ውስጥ ሴቶች በፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዳይሳተፉ የሚገድቡ የወንድ የበላይነትን የሚያስጠብቁ ስርዓቶች ቢኖሩም ሴቶች ወይም የአናሳ ቡድኖች አባላት ድምጽ ከመስጠት ወይም በፖለቲካ ከመሳተፍ የሚያግዳቸው ህግ የለም። በቁጥር ደረጃ የሴቶች ውክልናቢጨምርም እንኳን፣ የተመራጭ እና የተሹዋሚ ሴቶች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ አነስተኛ ነው። በጥቅምት 2012 ጠቅላይ ሚኒስትሩ 10 የሴት ሚኒስትሮች ያሉበትን አዲስ ካቢኔ አዋቅረዋል ወይም ከሞላ ጎደል የካቢኔው ግማሽ እንደሆኑ አሳውቀዋል። በተጨማሪም፣ በጥቅምት 2012 ሳህለወርቅ ዘውዴ የሐገሪቱ የመጀመሪያ የሴት ፕሬዘዳንት ሆነዋል። የሳህለወርቅ ዘውዴ ሹመት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአስተዳደራቸው ውስጥ የሴቶችን አቅም ለማጎልበት ከገለፁት ግብ ጋር የተጣጣመ ነበር። በሕዳር ወር ፓርላማው የሐገሪቱን የመጀመሪያ ሴት የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዘዳንት ቃለ መሐላ አስፈፀመ። በብሔራዊ ፓርላማ ውስጥ ሴቶች 38 በመቶ መቀመጫዎች ማለትም ከ547 ውስጥ 211 ይዘዋል።

የመንግስት የብሔር ፌዴራሊዝም ፖሊሲ በፌዴሬሽን ም/ቤት (በላይኛው የፓርላማ ምክር ቤት) ለሁሉም ብዙኃን የብሔር ቡድኖች ውክልና ለመስጠት የተናጠል የምርጫ ክልሎችምስረታን አስከትሏል። መንግስት ከ80 በላይ ለሆኑ ብሔረሰቦች እውቅና የሚሰጥ ሲሆን ፣ በፌዴሬሽን ምክር ቤት እያንዳንዱ "ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ እና ህዝብ" ቢያንስ በአንድ አባል እንደሚወከል ህገ መንግስቱ ይገልጻል።

ክፍል 4፡ በመንግስት ውስጥ ሙስና እና የግልጽነት እጦት

ህጉ ለሙስና ጥፋት የወንጀል ቅጣቶችን ይደነግጋል። መንግስት ህጉን በተሳካና በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አላደረገም። መንግሥት ባለሥልጣናት በይበልጥ በኃላፊነት የሚጠየቁበትን አዲስ ፖሊሲዎች አውጥቷል። እዚህም እዚያም በመንግሥት ባለሥልጣናት የሚፈጸሙ ሙስናዎች ሪፖርት ተደርገዋል። የመንግሥት ባለሥልጣናት አንዳንድ ጊዜ በሙስና ላይ ቢሳተፉም እንኳን በጥፋታቸው ግን ሲጠየቁ አይታይም።

ነሐሴ 12 ቀን የሥነ ምግባር እና የጸረ ሙስና ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ የፋይናንስ ደህንነት ማዕከል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል፤ ዓላማውም ሁለቱ ኤጀንሲዎች ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውርን፣ ለሽብርተኝነት የሚደረግ የፋይናንስ ድጋፍ እና ሌሎች ሙስናን የሚደግፉ ገንዘብ ነክ ወንጀሎችን በተሻለ መለየት እንዲችሉ ማድረግ ነው።

መጋቢት 29 ቀን አገሪቱ እ.ኤ.አ የ2020 የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅን አውጥታለች። ይህ የአገሪቱ የመጀመሪያ ሕግ ተራ ዜጎች የፌደራል መንግሥት ኤጀንሲዎች የሚወስዷቸውን እርምጃዎች፣ ውሳኔዎች እና ደንቦች በተመለከተ በፍርድ እንዲታይላቸው ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች አቤት እንዲሉ የሚያስችል ነው። የፌዴራል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ዓላማ የፌደራል መሥሪያ ቤቶች ግልጽነት እና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው እና ዜጎችም የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች ዋነኛውን ተልዕኳቸውን ከሳቱ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አስተዳደራዊ ማስተካከያ እንዲደረግላቸው ዕድል የሚያገኙበት ነው። ዜጎች እነዚህ መሥሪያ ቤቶች ሕጉን እንዲከተሉ ማስደረግ ብቻ ሳይሆን የገንዘብ ካሣ እንዲከፈላቸውም ሊጠይቁ ይችላሉ።

ሙስና፡- በመስከረም ወር መጨረሻ አካባቢ ፌዴራል ፖሊስ የትምህርት ሚኒስቴር ሹሞች የሆኑትን መኮንን አዲስ፣ እሸቱ አስፋው፣ ታዬ መንግሥቱ እና ንጉሤ በየነን የብር 280 ሚሊዮን (7 ሚሊዮን ዶላር) ኪሣራ እንዲደርስ እና የመጻሕፍት ሕትመት የጨረታ ሰነዱን መስፈርቶች የማያሟላ እንዲሆን አድርገዋል በሚል በቁጥጥር ስር አውሏቸዋል። ፖሊስ ከእነዚህ አራት የጨረታ ኮሚቴ አባላት መኖሪያ ቤቶች የውጭ አገር እና የአገር ውስጥ ገንዘብ ወርሷል። እንዲሁም ፖሊስ የእነዚህ አራት ግለሰቦች ዘመዶች ሒሳቦች እንዲታገዱ አድርጓል።

እንዲሁም መንግሥት የቀድሞው የብረታብረት እና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተር በነበሩት ክንፈ ዳኘው ላይ በመሠረተው ክስ ቀጥሎበታል፤ እኚህ ግለሰብ በ2010 በቁጥጥር ሥር የዋሉ ነበሩ። ዓቃቤ ሕግ እና መርማሪዎች ከ80 ቢሊዮን ብር (ከ2 ቢሊዮን ዶላር) በላይ ለሆነ ገንዘብ አጠራጣሪ የግዢ ሂደት አጋልጠዋል። በጥር 2011 ክንፈ በልደታ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዲስ አበባ ውስጥ አራት የሙስና ክስ ቀርቦባቸዋል። በዓመቱ መጨረሻ ክሱ ቀጥሏል።

ሐብት ማሳወቅ ፡- የአገሪቱ የሥነ ምግባር እና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን የመንግሥት ሠራተኞች ሃብታቸውን የሚያሳውቁበትን አሠራር በመዘርጋት የጸረ ሙስና ፖሊሲያቸውን እና የሕግ ማስከበር ሥራቸውን ይበልጥ አጠናክረዋል። ከነሐሴ ወር በፊት ኮሚሽኑ ሥልጠናው በከፍተኛ ባለሥልጣናት ላይ እንዲያተኩር አድርጎ ነበር። ከዚያ በማስከተል ስለ ሃብት ማሳወቅ ሂደት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ሥልጠናውን አስፋፍቶ ለሠራተኞች ሰጥቷል። በነሐሴ 18 ቀን አብዛኞቹ ሕግ አውጪዎች ተመዝግበው ሀብታቸውን ለኮሚሽኑ አሳውቀዋል። ነሐሴ 22 ቀን ኮሚሽኑ ሃብታቸውን ያላሳወቁ እና የወንጀል ክስ ሊቀርብባቸው የሚችሉ 184 የፌዴራል እና የአዲስ አበባ ባለሥልጣናትን ዝርዝር ለፖሊስ ልኳል።

ክፍል 5፡ ተፈፀሙ በተባሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ አለምአቀፋዊና መንግስታዊ ያልሆነ ምርመራን በተመለከተ መንግስት ያለው አመለካከት

ልዩ ልዩ የአገር ውስጥ እና ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቡድኖች በአጠቃላይ በመንግሥት ገደብ ሳይጣልባቸው ሲሰሩ የቆዩ ሲሆን፤ ምርመራዎችን በማካሄድ በሰብዓዊ

መብቶች ጉዳዮች ላይ ግኝቶቻቸውን ያሳትማሉ። የመንግሥት ኃላፊዎችም ለእነርሱ አስተያየቶች ትብብር ሲያደርጉ እና ምላሽም ሲሰጡ ነበር።

የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች (CSO) ዘርፍ መስፋፋቱን ቀጥሎ ብዙዎች የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ለመመስረት ሲመዘገቡ ቆይተዋል። የአገር ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች አቅም አሁንም ተግዳሮት ሆኖ ቀጥሏል። በ2012 ውስጥ የተካሄዱ ማሻሻያዎች የአገር ውስጥ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እንዲጎለብቱ ድጋፍ አድርጓል። ሕጉ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው በጎ ፈቃደኞች በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ውስጥ እስከ አንድ ዓመት ድረስ እንዲሰሩ ይፈቅዳል።

ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ቡድኖች በአገሪቱ ውስጥ በመዘዋወር ምርመራ እንዲያካሂዱ እና ሪፖርት እንዲያቀርቡ ፈቃድ ያገኙ ቢሆኑም እንኳን ፣ ከመንግሥት የተደረገላቸው አቀባበል ቀዝቀዝ ያለ ነበር። በርካታ ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶች ከአርቲስት እና አክቲቪስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያ በኋላ በአገሪቱ የተከሰተውን ረብሻ በተመለከተ ሪፖርቶች አውጥተዋል። እነዚህ ሪፖርቶች እንዳመለከቱት የጸጥታ ኃይሎች የኦሮሞ ሲቪሎችን ዒላማ አድርገዋል። አንድ ሪፖርት የተከሰተውን ረብሻ በተመለከተ በበይነ መረብ ቪድዮ አዘጋጅቶ አቅርቧል። ነሐሴ 12 ቀን ዓቃቤ ሕጉ "ዓለም ዓቀፉ ማህበረሰብበአገሪቱ ውስጥ ላለው ውስብሰብ እና ተለዋዋጭ ሁኔታ ምንም ዓይነት ትኩረት አልሰጠም" በማለት ምላሽ ሰጥቷል። በግንቦት ወር አምነስቲ ኢንተርናሽናል በ2012 በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች በተወሰኑ የኦሮሚያና የአማራ ክልሎች ውስጥ ተፈጸሙ በተባሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ ሪፖርት አውጥቷል። አምነስቲ አንተርናሽናል በ2012 ስለተፈናቀሉ በሺዎች ስለሚቆጠሩ ተፈናቃዮች መንግሥት የሰጠው ምላሽ አነስተኛ ነው በሚል አውግዟል። የአማራ እና የኦሮሚያ ክልሎች ባለስልጣናት ሪፖርቱ ሚዛናዊነት የጎደለው ነው ሲሉ ምክንያታቸው ሪፖርቱ በእነዚህ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ቡድኖች የፈጸሟቸውን አሰቃቂ ወንጀሎች ያላካተተ ነው የሚል ነበር። ግንቦት 24 ዓቃቤ ሕግ አዳነች አቤቤ በትዊተር ገጻቸው እንዳመለከቱት በአምነስቲ ሪፖርት የተካተቱትን ክስተቶች አስመልክቶ መንግሥት የራሱን ምርመራ መጀመሩን ገልጸዋል።

ባለሥልጣናት በአንድ አካባቢዎች የሰብዓዊ መብቶች ድርጅቶችን፣ የሚድያዎችን፣ የሰብዓዊ ድጋፍ ኤጀንሲዎችን እና የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችን እንቅስቃሴዎች ገደብዋል።

በእነዚህ አካባቢዎች ደግሞ በኦነግ-ሸኔ እና በመንግሥት የጸጥታ አገልግሎቶች መ ካ ከል ይፋዊ ግጭት ይካሄድ ነበር። (በክፍል 2.ሀ የሲቪል ነጻነትን ማክበር -- ሃሳብን በነጻነት መግለጽ -- መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተጽዕኖ የሚሉትን ክፍሎች ይመልከቱ)።

<u>የመንግሥት የሰብዓዊ መብቶች አካላት፡-</u> የእምባ ጠባቂ ተቋም ሥራ አስፈጻሚው የመንግሥት ቅርንጫፍ እና ባለሥልጣናት የሚፈጽሟቸውን አስተዳደራዊ ጉድለቶችን እና የእስር ቤት ሁኔታዎችን የሚመለከቱ ቅሬታዎችን የመመርመር ሥልጣን አለው። በ2012 ፓርላማው እ.ኤ.አ. ከ2000 ጀምሮ ሥራ ላይ የነበረው የቀድሞ አዋጅ በመሻር ፣ የእምባ ጠባቂ ተቋምን የሚያቋቁም አዋጅ አጽድቋል። ይህ አዋጅ የውጭ አገር ዜጎች ለመሥሪያ ቤቱ አስተዳደራዊ እና የመብት ጥሰትን አስመልክቶ አቤቱታ የማቅረብ መብት ይሰጣቸዋል።

የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ገለልተኛ የመንግስት ተቋም ሲሆን፣የአገሪቱን ሰብዓዊ መብቶች በተመለከተ የመመርመር እና ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። ፓርላማው የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንን እ.ኤ.አ. በ2000 ያቋቋመ ሲሆንለኮሚሽኑ ገንዘብ መመደብ እና እንቅስቃሴውንም በበላይነት መቆጣጠሩን ቀጥሎበታል። ለዚህ ተቋም ይበልጥ ነጻነት ለመስጠት አዲስ ሕግ ወጥቷል (ክፍል 1.ሠ. የሰውን ክብር መጠበቅ፣ ፍትሐዊ ግልጽ የፍርድ ሂደትን መከልከል፣ የፍትሐ ብሔር የፍርድ ሂደቶች እና መፍትሔዎች የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)። በሰኔ ወር ፓርላማው ለኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ምርጫዎችን እንዲታዘብ እና በኮቪድ-19 የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት የሰብዓዊ መብት ሁኔታዎችን እንዲከታተል በድምፅ ሥልጣን ሰጠ። በሐምሌ ወር ፓርላማው የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ከፍተኛ ሠራተኞች እንደ ሙሉ ሰዓት ወይም ቋሚ ሠራተኞች ክፍያ እንዲመደብላቸው የሚደነግግ ሕግ አወጣ። የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ከ40 በላይ በሆኑ ስፍራዎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን መርምሯል። የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን መንግሥት በመስከረም ወር የልደቱ አያሌውን የሰብዓዊ መብት ጥሰት እና እስር በተመለከተ የሕግ የበላይነትን ወደ ጎን ትቷል የሚል መግለጫ ቢያወጣም እንኳን ከመንግሥት በኩል የገጠመው አሉታዊ እርምጃ የለም። እንዲሁም የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በኮቪድ-19 የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት ማለትም በሚያዝያ ወር መንግስት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ፈጽሟል የሚል ትችት አቅርቧል።

ክፍል 6፡ አድልዎ ፣ ማህበራዊ በደሎች እና ህገወጥ የሰዎች ዝውውር

ሴቶች

መድፈር እና በቤት ወስጥ የሚፈጸም የኃይል ድርጊት፡- በሕጉ አስገድዶ መድፈር በወንጀልነት የተፈረጀ ሲሆን፣ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ሰው ላይ የጥፋቱን ክብደት ከግምት በማስገባት ከአምስት እስከ 20 ዓመት የሚደርስ እስር ሊያስከትል ይችላል። ሕጉ በትዳር ጓደኛ ላይ ስለሚፈጸም የአስገድዶ መድፈር ወንጀል በግልጽ ያስቀመጠው ድንጋጌ የለም። መንግሥት ሕጉን ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ አላደረገም። ሕጉ በትዳር ጓደኛ ወይም በባልና ሚስትነት አብረው የሚኖሩ አጋሮችን በተመለከተ የሚፈጸምን የኃይል ድርጊት የሚደነግገው በትዳር ጓደኛ ላይ የሚፈጸምን የመድፈር ድርጊት ሳያካትት ነው። አንዳንድ ዳኞች ይህንን ድንጋጌ በትዳር ጓደኛ ላይ ለሚፈጸም የመድፈር ተግባር ተፈጻሚነት አለው በማለት ይተረጉሙታል፤ ነገር ግን ሌሎች እንዲህ ላለው ጉዳይ ትኩረት አልሰጡም ።

የትግራይ ሴቶች ማኅበር በሚያዝያ እና በግንቦት ወራት መካከል በ133 ልጃገረዶች ላይ የወሲብ ጥቃት መፈጸሙን ዘግቧል። በተመሳሳይ ወቅት የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ሕጻናት እና ወጣቶች ጉዳዮች ቢሮ ከሦስት ሆስፒታሎች 101 የሕጻናት መደፈር ዘገባ ደርሶታል። ይህንን ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ሪፖርት ተከትሎ መንግሥት እና የሲቪል ሶሳይቲ ድርጅቶች በአስገድዶ መደፈር እና በወሲብ ጥቃት ጉዳዮች ዙሪያ ባከናወኗቸው ተግባራት የሪፖርት አደራረግ እና የሕግ ማስከበር ሥራዎች ተሻሽለዋል፤ ለተጎጂዎችም የሥነ ልቦና ድጋፍ ተሰጥቷል። የየክልሉ የሴቶች እና እና ሕጻናት ጉዳዮች ቢሮዎች ተጠርጣሪዎችን ለሕግ ለማቅረብ ከፖሊስ ጋር ሰርተዋል፤ ነገር ግን በሕበረተቡ ዘንድ ስለ ሕጉ ያለ ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ እና ለመመስከር ፈቃደኛ የሆኑ ግለሰቦች ማግኘት አስቸጋሪ በመሆኑ እነዚህ ጥረቶች ያስገኙት ውጤት አነስተኛ ነው። የአገር ውስጥ ሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በጾታ ላይ የተሰመረተ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጠቂዎች ድጋፍ ሰጥተዋል። የተባበሩት መንግሥታት በሥነ ተዋልዶ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኘው ሜሪ ስቶፕስ ኢትዮጵያ ሁለት ቀጥተኛ የስልክ መስመሮች እንዲያዘጋጅ እና የጾታ ጥቃት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች የምክር አገልግሎቶች እንዲሰጥ እገዛ አድርጓል።

የቤት ውስጥ የኃይል ድርጊት ሕገ ወጥ ቢሆንምመንግሥት ሕግን ለማስከበር የሰራው ሥራ ወጥነት የጎደለው ነው። በሚደርሱ ጉዳቶች ክብደት ላይ በመመስረት ጥፋተኛ ሆነው በሚገኙ ሰዎች ላይ የሚጣለው ቅጣት ከአነስተኛ የገንዘብ ቅጣት እስከ 15 ዓመት እስር ነው። በትዳር ጓደኛ ላይ የሚፈጸም የኃይል ተግባርን ጨምሮ የቤት ውስጥ የኃይል ድርጊት በሰፊው የሚታይ ማኅበራዊ ችግር ነው። እ.አ.አ. በ2016 በወጣው *የሥነ ሕዝብ እና የጤና ዳሰሳ*መሠረት፣ ዕድሜያቸው ከ15 እስከ 49 የሚደርስ ትዳር ከመሰረቱ ሴቶች እና ልጃገረዶች መካከል 34% የሚሆኑት ከባለቤቶቻቸው አካላዊ፣ ወሲባዊ እና ሥነ ልቦናዊ ጥቃት ደርሰባቸዋል።

<u>የሴት ልጅግርዛት</u> ፡- የሴቶች ግርዛት ሕገ ወጥ ሲሆን ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ሰው ላይ እስከ ሦስት ወር የሚደርስ እስራት ወይም የገንዘብ ቅጣት ይደነግጋል። እጅግ አሰቃቂ የሴቶች ግርዛት ዓይነት የሆነውን የውጨኛውን የሴት ልጅ ብልት ክፍል ቆርጦ በማንሳት የተከሰሰሰው ከ5 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል። ከመንግሥት በተገኙ መረጃዎች መሠረት በሴቶች ግርዛት ምክንያት የቀረበ ክስ የሌለ ሲሆን እንደ ሚዲያ ዘገባ ደግሞ ይህ የሆነበት ምክንያት ሕጉ ተፈጻሚ ባለመደረጉ ነው።

የዩኑሴፍ የሴቶች ግርዛት ፕሮፋይል እንደሚያሳየው ዕድሜያቸው ከ15-49 ከሆነ ሴቶች መካከል 65 በመቶ የሚሆኑት ተገርዘዋል። የሴቶች ግርዛት በከፍተኛ ደረጃ የሚታየው በሶማሌ ክልል ሲሆን (99 በመቶ)፣ ዝቅተኛው ደግሞ በትግራይ ክልል ነው (23 በመቶ)። እንደ ዩኒሴፍ ከሆነ የሴቶች ግርዛት በአገሪቱ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰው በኦሮሚያ ክልል ነው። ነገር ግን እንደ ዩኒሴፍ ሪፖርት የሴቶች ግርዛት በሶማሌ ክልል ጉልህ ለውጥ አላሳየም። በከተማ አካባቢዎች ያነሰ ነው።

<u>ሌሎች ጎጂ ባሕላዊ ድርጊቶች</u>፡- በጠለፋ ጋብቻን መፈፀም ህገ ወጥ ነው። ድርጊቱን ለማስቆም የመንግስት ጥረት ቢኖርም፣ በአንዳንድ ክልሎች ድርጊቱ ቀጥሏል። በሚያዝያ እና በግንቦት ወራት መካከል በኮቪድ-19 ምክንያት ትምህርት ቤቶች በመዘጋታቸው አስገድዶ ጋብቻ ለመፈጸም በአገሪቱ ውስጥ ጠለፋ በከፍተኛ ደረጃ ጨምሯል። በአብዛኛዎቹ የጠለፋ ጋብቻዎች ግዳጅ ወሲባዊ ግንኙነቶች የሚፈጸምባቸው ሲሆን፣ ሴቶች ብዙውን ጊዜ በጠለፋው ወቅት አካላዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል።የጠለፋ ተግባራት በቤተሰቦች፣

በማህበረሰቦች እና በጎሳ ቡድኖች መካከል ግጭቶችን ያስከትላሉ። ጠለፋ ተፈጽሞ ተበዳይዋ አጥቂውን ለማግባት ከተስማማች አጥፊው ወገን ቅጣት አይደርስበትም።

<u>ወሲባዊ ትንኮሳ፡</u>- ወሲባዊ ትንኮሳ በሰፊው ታይቷል። ህጉ በተከሳሽ ላይ ከ18 እስከ 24 ወራት የሚደርስ ቅጣትን የሚጥል ሲሆን ባለስልጣናት ግን በአብዛኛው ህጉን አላስከበሩም። መንግሥትበመስከረም 2012 በተሻሻለው የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕግ ውስጥ በሥራ ቦታ የሚፈጸሙ የወሲብ ጥቃቶችን እና የኃይል ድርጊቶችን የሚመለከት ደንብ አካቷል።

<u>የህዝብ ብዛትን በመቆጣጠር ረገድ የሚኖር ግዳጅ፡</u>- በመንግሥት በኩል በግዴታ ስለተፈፀመ የጽንስ ማስወረድ ወይም ያለ ውዴታ መካን ስለመደረግ ሪፖርቶች አልነበሩም።

<u>መድልዎ</u> ፡- በሴቶች ላይ የመድልዎ አሠራር በሰፊው ይታይ ነበር ። በተለይ ከጠቅላላው ሕዝብ መካከል በግምት 80 በመቶ የሚሆነው በሚኖርበት በገጠሩ አካባቢ በከፍተኛ ደረጃ ታይቷል። ሕጉ አድሎአዊ የሆኑ ደንቦች የተካተቱበት ሲሆን ፣ ለምሳሌ በሕጉ ባልን የቤተሰብ መሪ በማድረግ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በላይ ለሆናቸው ልጆች እንደ ብቸኛ አሳዳጊ ይወሰዳል። ፍርድ ቤቶች በቤት ውስጥ የሚፈጸም የኃይል ጥቃትን ለፍቺ እንደ በቂ ምክንያት አላዩትም። ምንም ያህል ጊዜ በትዳር አብረው ቢቆዩ፣ ምንም ያህል ልጆች ቢያሳድጉ እና የጋራ ንብረት ቢያፈሩ ግንኙነታቸው ከተቋረጠ ሕጉ ለሴቶች የገንዘብ ድጋፍ እንዲደረግ የሚያዘው ለሦስት ወራት ብቻ ነው። አንደ ባልና ሚስት መኖር ተብሎ ለሚታወቀው የተለምዶ የጋብቻ ዓይነት ሕጉ የሚሰጠው ስፍራ የተወሰነ ነው። እንደ ባልና ሚስት በሚኖሩ ባለትዳሮች ባል ለቤተሰቡ የገንዘብ ድጋፍ የማድረግ ግዴታ የለበትም፤ በዚህም ምክንያት ሴቶች እና ልጆች አንዳንድ ጊዜ ያለ ረዳት ይቀራሉ። ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች በኢኮኖሚያዊ እና በማኅበራዊ ግንኙነት ጉዳዮች ላይ ባሕላዊ ሕግ ተፈጻሚ ያደርጋሉ።

ሁሉም የፌዴራል እና የክልል የመሬት ሕግጋት ሴቶች የመንግሥት መሬት እንዲያገኙ መብት ይሰጣቸዋል። የውርስ ሕጎች ደግሞ ባሎቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች በጋብቻ ወቅት ካፈሯቸው ንብርቶች መካከል ግማሹን እንዲወርሱ ይፈቅዳሉ፤ ሆኖም ግን የሁለቱም የሕግ ድንጋጌዎች አፈጻጸም ወጥነት አልነበረውም።

በውስን የትምህርት ዕድሎች እና ስለሴቶች ቅጥር በሕግ በተቀመጡ ገደቦች ምክንያት ጠቃሚ ሥራዎች፣ ብድር እና የንግድ ባለቤትነት ለሴቶች ያላቸው ተደራሽነት ውስን ነበር። ከእነዚህ ገደቦች መካከል አደገኛ ተብለው በሚፈረጁ ሥራዎች ለምሳሌ በማዕድን ማውጣት እና በግብርና ሥራ ላይ ያሉ ገደቦችን ያካትታሉ። ሴቶች በእነዚህ ወሳኝ በሆኑ የኢኮኖሚ ራስን የመቻል ዕድሎች ይበልጥ መጠቀም እንዲችሉ ለማድረግ በመካሄድ ላይ ያሉ በርካታ ሥራዎች አሉ።

ልጆች

<u>የልደት ምዝገባ፡-</u> የአንድ ህጻን ዜግነት የሚገኘው ከወላጆች ነው። ህጻናት ሲወለዱ እንዲመዘገቡ ህጉ ያዝዛል። በሆስፒታሎች ውስጥ የሚወለዱ ህጻናት ተመዝግበዋል፤ ከሆስፒታሎች ውጭ የሚወለዱት አብዛኛዎቹ አልተመዘገቡም። በተለይ በገጠር አካባቢዎች እጅግ በጣም አብላጫ ቁጥር ያላቸው ህጻናት የሚወለዱት በቤት ውስጥ ነበር። ህጻናትን አለማስመዝገብ ህዝባዊ አገልግሎቶችን የሚያሳጣ መሆኑን መንግስት ኣሳውቆ የልደት ምዝገባዎችን ለመጨመር በ2009 ተጀምሮ የነበረው ዘመቻ ቀጥሏል።

<u>ትምህርት፡-</u> ህጉ ትምህርትን የግዴታ አያደርገውም። የ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ዓለም አቀፍ እና ከክፍያ ነፃ ቢሆንም በተለይ በገጠር አካባቢዎች የሐገሪቱን ወጣቶች የሚያስተናግዱ በቂ ት/ቤቶች የሉም። የመማሪያ ቁሳቁሶች ወጪ ለብዙ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ማስተማር አስቸጋሪ እንዲሆን አድርጎባቸዋል። በዓመቱ ውስጥ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሁሉም የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ተማሪዎች የደንብ ልብሶችን እና የመማሪያ ቁሳቁሶችን አድሏል። ሊገኝ በቻለው የቅርብ ጊዜ መረጃ መሠረት ከወንዶች ልጆች መካከል 90 በመቶ እና ከሴቶች ልጆች ደግሞ 84 በመቶ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመዝግበዋል።

<u>የህጻናት ጥቃት :-</u>የሕጻናት ጥቃት የተስፋፋ ነበር። እንጥል መቁረጥ፣ ጉሮሮ መቧጠጥ እና የወተት ጥርስ መንቀል በጣም ከተስፋፉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መካከል ነበሩ። በህጻናት ላይ የወሲብ ጥቃት በመፈፀም ተግባር ላይ መንግስት ቅጣት መጨመሩን በአፋሪካ ቻይልድ *ፖሊሲ ፎረም የሚታተመው የ2006 የህጻናት ደህንነት አፍሪካ ሪፖርት*

አረጋግጧል። "ለህጻናት የተመቹ" ችሎቶች በህጻናትና በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን አዳምጠዋል።

<u>በልጅነት፣ ያለ ዕድሜ እና የግዴታ ጋብቻ</u>፡- ህጉ ለሴቶችና ለወንድ ልጆች የጋብቻ እድሜ 18 ዓመት መሆኑን አስቀምጧል። ይሁን እንጂ ባለስልጣናት ይህንን ህግ በወጥነት የማያስከብሩ ሲሆን የገጠር ቤተሰቦችም አንዳንድ ጊዜ ድንጋጌው ስለመኖሩ ግንዛቤው የላቸውም። እ.ኤ.አ. በ2016 በዩኒሴፍ በወጣ መረጃ መሠረት ዕድሜያቸው ከ20 እስከ 24 ከሆኑ ሴቶች መካከል 40 በመቶ የሚሆኑት ከ18 ዓመት ዕደሜያቸው በፊት ያገቡ ናቸው፤ 14 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ከ15 ዓመት ዕድሜ በፊት አግብተዋል።

መንግሥት የኮቪድ-19ን ስርጭት ለመከላከል ልዩ ልዩ እርምጃዎችን ወስዷል። ከእነርሱም መካከል አንዱ ሁሉንም ትምህርት ቤቶች መዝጋት ነው። የትምህርት ቤቶች መዘጋት በገጠር አከባቢዎች እንደ ደህንነት መረብ የሚያገለግለውን የህፃናት ጋብቻ ልምዶችን አስቀድሞ የመለየት የመምህራን ሚና አስቀርቷል። የትምህርት ቤቶች መዘጋት እና ተማሪዎች በየቤቶቻቸው እንዲቆዩ የተሰጠው ምክር የልጅነት ዕድሜ ጋብቻ በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር አድርጓል። በሚያዝያ እና በግንቦት ወራት መካከል በአማራ ክልል 249 ዕድሜያቸው ከስምንት እስከ 15 የሆኑ ልጃገረዶች ተድረዋል። መንግሥት ከዕድሜ በታች ጋብቻ ሲፈጸም ይህንን ለመፍታት ተግባራዊ የሚያደርገው ዘዴ በዳዮችን ከመቅጣት ይልቅ በትምህርት እና በሽምግልና ላይ ያተኮረ ነው።

<u>በልጆች ላይ የሚፈጸም የወሲብ ብዝበዛ፡-</u> ወሲብን በስምምነት ለመፈፀም የተቀመጠው አነስተኛ ህጋዊ የእድሜ መጠን 18 ዓመት ቢሆንም ባለስልጣናት ይህንን ህግ አላስከበሩም። ከህጻናትልጆች ጋር የወሲብ ግንኙነት በሚፈፅም ላይ ህጉ ከሶስት እስከ 15 ዓመት እስር ይደነግጋል። ከህጻናት ጋርየሚፈፀሙ የወሲብ ግንኙነቶችን የሚያሳዩ የብልግና ፅሑፎችን እና ስዕሎችን በሚያዘዋውሩ ላይ ህጉ የአንድ ኣመት እስርና ከፍተኛ የሚባል መጠን ያለው የገንዘብ መቀጫ ይደነግጋል። በየካቲት ወር ፓርላማው አዋጅ ቁጥር 1178/2020ን አጸደቀ፤ ይህ አዋጅ የሰዎችን ሕገ ወጥ ዝውውር እና ሰዎችን ሸሽጎ ማሳለፍን ለመከላከል እና ለማስቆም የወጣ ነው፤ ይህም ሕግ ሁሉንም አይነት ሕጻናትን ለወሲብ በሕገ ወጥ መንገድ የማዘዋወር ተግባራትን ይከለክላል። አንዳንድ ቤተሰቦች እና ሴተኛ አዳሪዎች የሚገኙባቸው ስፍራዎች ድህነት ከሰፈነባቸው የአገሪቱ ገጠራማ አካባቢዎች የሚመጡ ልጃገረዶችን በቤት

ውስጥ ሠራተኛነት እና በሴተኛ አዳሪነት ያሰማራሉ። በአዲስ አበባ ማዕከላዊ ገበያ አንዳንድ የሴተኛ አዳሪዎች ቤቶች ባለቤቶች ልጃገረዶችን እንደበዘበዙ የሚያሳዩ ዘገባዎች አሉ።

<u>ጨቅላ ህጻናትን መግደል ወይም የአካል ጉድለት ያለባቸውን ጨቅላ ህጻናት መግደል</u>፡- የአካል ጉድለት ያለባቸውን ጨቅላ ህጻናት ጨምሮ በመንፈሳዊ ስርዓት እና በባዕድ አምልኮ ላይ የተመሰረተ የጨቅላ ህጻናት ግድያ ራቅ ባሉ የጎሳ አካባቢዎች በተለይም በደቡብ ኦሞ የቀጠለ ተግባር ነው። የአካባቢው መንግስታት ይህን ልማድ እንዲያስቀሩ ማህበረሰቦችን ለማስተማር ጥረዋል።

<u>ተፈናቃይ ልጆች፡-</u> በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር የ2003 ሪፖርት መሰረት ወደ 150ሺህ የሚገመቱ ልጆች የጎዳና ላይ ተዳዳሪ ነበሩ። ከነርሱ መካከል 60ሺህ ያህሉ በዋናው ከተማ ውስጥ ነበሩ። የወላጆች መታመምወይም ገቢ በማነሱ ምክንያት ልጆችን መርዳት ባለመቻላቸው ለዚህ እንደዳረጋቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ይገልጻል። ፈጣን የከተማ መስፋፋት፣ ህገ ወጥ የስራ ቅጥር ደላሎች፣ በከተሞች ውስጥ የተሻለ ኑሮ የማግኘት ከፍተኛ ተስፋ እና ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት ችግሩን እንዳባባሰ በ2007 በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተደረገው ጥናት ያስገነዝባል። እነዚህ ልጆች አብዛኛውን ጊዜ ይለምናሉ፣ አንዳንዴ የወሮበላ ቡድን አካል ይሆናሉ ወይም ህጋዊ ባልሆነ የስራ ዘርፍ ይሰማራሉ።

መንግሥት አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ የጎዳና ልጆች ብዛት አሳስቦታል። መንግሥት ችግረኛ ልጆችን መልሶ ለማቋቋም ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በጋራ ሰርቷል። የጎዳና ልጆችን መልሶ ማቋቋሚያ ማዕከል ለአዲስ አበባ ሠራተኛ እና ማኅበራዊ ጉዳዮች ቢሮ በእርዳታ መልክ ተሰጥቷል። ማዕከሉ እስከ 2000 የሚሆኑ ልጆችን ያስተናግዳል፤ ተጠቃሚዎች የአጭር ጊዜ ሥልጠና፣ የሥነ ልቦና ሕክምና እና የሙያ ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል። እንዲሁም መንግሥት ትምህርታቸውን መቀጠል ለሚፈልጉ የጎዳና ልጆች እገዛ አድርጓል።

<u>በተቋም ውስጥ ያሉ ህጻናት፡-</u> በዩኒሴፍ በታተመው ስታቲስቲክስ መሰረት በ2004/2005(2012) በሐገሪቱ ውስጥ 4.5 ሚሊዮን፣ ማለትም ከህዝቡ 4.9 በመቶ የሚሆኑ ወላጅ አልባ ልጆች እንደነበሩ ተገምቷል። እጅግ ብዙዎቹ ከሩቅ ዘመዶቻቸው ጋር ይኖራሉ። መንግስታዊና በግል የሚንቀሳቀሱ የወላጅ አልባ ህጻናት ማሳደጊያዎች ከመጠን

በላይ የተጣበቡ ሲሆኑ ብዙውን ጊዜ ንጽህና የጎደላቸው ነበሩ። በተቋም ውስጥ ያሉ ልጆች በቂ የጤና እንክብካቤም አላገኙም።

<u>አለምአቀፍ የሕጻን ልጅ ጠለፋዎች/አፈናዎች</u>፡- ሐገሪቱ የ1972 (1980) በአለምአቀፍ የህጻን ልጅ ጠለፋ ሕዝባዊ ገጽታዎች ላይ የሚያተኩረው የሄግ ስምምነት አባል አይደለችም። ታኅሳስ 30 ፓርላማው የቤተሰብ ሕግን ሰፋ ባለ መልኩ ከማሻሻል ጋር በተያያዘ ድንበር ዘለል ጉዲፈቻን የሚያግድ ሕግ አጸደቀ። *በአለም አቀፍ በወላጅ በሚካሄድ የሕፃናት ጠለፋ ላይ የአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን ዓመታዊ ሪፖርት ይመልከቱ።* https://travel.state.gov/content/travel/en/International-Parental-Child-Abduction/for-providers/legal-reports-and-data/reported-cases.html.

ፀረ-ሴማዊነት

የአይሁድ ማህበረሰብ ወደ 2,000 ገደማ አባላት ነበሩት። ፀረ-ሴማዊ ድርጊቶች ስለመፈፀማቸው ሪፖርቶች አልነበሩም። የአዲስ አበባ የአይሁድ ማህበረሰብ እምነቱን ለመተግበር የመንግስት ከለላ እንዳለው ያምን እንደነበር ሪፖርት አድርጓል። ነገር ግን የተወሰነ ማህበረሰባዊ መገለል ገጥሞታል።

ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን *ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሪፖርት ይመልከቱ።* https://www.state.gov/trafficking-in-persons-report/.

የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች

ህገ መንግስቱ የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የእኩል መብቶች እንዲኖር አያስገድድም ። አካላዊ እና አእምሮአዊ ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በስራ ቅጥር ረገድ አድሎዎ እንዳይደረግባቸው የቅጥር ህጉ ይከለክላል፤ ነገር ግን የአእምሮ ወይም የስሜት ህዋሳት ጉዳቶችን በግልጽ አይጠቅስም። መስማት ለተሳናቸው ሰዎች መኪና መንዳት ህገ ወጥ ነው፤ ነገር ግን መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር ላለፉት 45 ዓመታት መንጃ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ሲጠይቅ ቆይቷል።

ሕጉ በአካል ጉዳት ላይ በመመስረት በሥራ ቅጥር ላይ መድልዎ ማድረግን ይከለክላል። እንዲሁም አሰሪዎች አግባብነት ያለውን የሥራ ወይም የሥልጠና ሁኔታዎችን እና ማቴሪያሎችን የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች እንዲያመቻቹ ይጠይቃል። በተለይ ሕጉ የአካል ጉዳት ባለባቸው ሴቶች ላይ ላለው ጫና ዕውቅና ይሰጣል።

ሕጉን ለመተግበር መንግስት አንዳንድእርምጃዎችን ወስዷል። ለምሳሌ ያህል፤ መስማት ለተሳናቸው እና የመስማት ችግር ላለባቸው የመንግስት ሠራተኞች አስተርጎሚዎችን በመመደብ። ጉዳት ላለባቸው ግለሰቦች የቅጥር ሕጎችን በሚመለከት የሚቆጣጠሩት በሠራተ ኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና የሕዝብ አገልጋዮች አስተዳደር ኮሚሽን ነበሩ።

ሕጉ ሕንጻዎች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እንዲሆኑ የሚደነግግ ቢሆንም እንኳን እነዚህን ስርዓቶች በግልጽ የሚያስቀምጡ ደንቦች የሉም። ሕንጻዎች እና መጸዳጃ ቤቶች ብዙውን ጊዜ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ አይደሉም። የሕንጻዎች ባለቤቶች የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች በምድር ቤት የአፓርታማዎች ምርጫ እንዲሰጧቸው ይጠበቅባቸዋል፤ እነርሱም በአጠቃላይ ይህንን አድርገዋል።

በተመድ የስነ-ህዝብ ፈንድ እና የስነ-ህዝብ ካውንስል ሪፖርት መሰረት የአካል ጉድለት ካለባቸው ሶስት ልጃገረዶች አንዷ ቢያንስ አንድ የወሲብ ጥቃት ይገጥማታል። በተጨማሪም አካል ጉዳት ያለባቸው ልጃገረዶች በቤታቸውና በማህበረሰባቸው ውስጥ ስልታዊ እና የኃይል ጥቃት የተሞላበት እንግልት ይገጥማቸዋል። ብዙዎቹ አካል ጉዳተኛ ልጃገረዶች ለየት ያሉ በመሆናቸው እንደሚነቀፉ እና በጥንቆላ/ ርግማን የተያዙ ተደርገው በመታየታቸው እንደሚወነጀሉ ሪፖርቱ ይገልፃል።

የአካል ጉዳት ያለባቸው ሴቶች በትምህርትና በስራ ቅጥር ተጨማሪ የከፉ ሁኔታዎችይገጥሟቸዋል። እ.አ.አ. በ2010 *(2002/2003) የስነ-ህዝብ ካውንስል የወጣት አዋቂዎች የዳሰሳጥናት* መሰረት፣ የአካል ጉድለት ከሌለባቸው 48 በመቶ ልጃገረዶችና 55 በመቶ ወንድ ልጆች ጋር ሲነፃፀሩ በትምህርት ቤት ውስጥ የነበሩት የአካል ጉዳተኛ ልጃገረዶች23 በመቶ ነበሩ።

በብሔራዊ ደረጃ መስማትና ማየት ለተሳናቸው ሰዎች በርካታ ትምህርት ቤቶች ያሉ ሲሆን፣ የአእምሮ ዕድገት ውስንነትላለባቸውም ልጆችና ወጣቶች በርካታ የሥልጠና ማዕከላት አሉ። ከ10 ክልሎችውሰጥ በአምስቱ የሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍ ማዕከላት የግንኙነት መረብአለ።

ሕጉ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች እንዳይመርጡ ወይም በሌላ መልኩ በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ እንዳይኖራቸው አይከለክልም፤ ሆኖም ግን የተደራሽነት ችግሮች ከፍ ያለ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች ተሳትፎ ይበልጥ አስቸጋሪ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል። አብዛኞቹ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ተደራሽ በመሆናቸው፣ እነዚህ ግለሰቦች እንዲሁም አዛውንቶች፣ ነፍሰ ጡር ሴቶች እና የሚያጠቡ እናቶች ድምጽ በሚሰጥበት ጊዜ በቅድሚያ እንዲስተናገዱ ተደርጓል።

ብሔራዊ የዘር/የጎሳ አናሳ ማህበረሰቦች ቡድኖች አባላት

እ.ኤ.አ. በ2007 ተካሂዶ በነበረው የሕዝብ ቆጠራ በአገሪቱ ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች ያሏት ሲሆን፣ ከእነዚያ መካከል የኦሮሞ ብሔር አባላት ከጠቅላላው ሕዝብ ከሞላ ጎደል 34 በመቶ በመሆኑ በቁጥር የመጀመሪያውን ደረጃ ይዟል። አከራካሪው ተከታዩ የሕዝብ ቆጠራ በ2012 እንዲካሄድ ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በቀጣይ እስኪገለጽ ድረስ እንዲራዘም ተደርጓል። የፌደራል ሥርዓቱ እና ሕገ መንግሥቱ የፖለቲካ ድንበሮችን ከብሔር አንጻር ያስቀምጣል፤ ነገር ግን ሰነዶች ራሳቸው የተዘጋጁት በነዚህ ድንበሮች ዙሪያ አይደለም። አብዛኞቹ የፖለቲካ ፖርቲዎች በዋናነት በብሔር ላይ የተመሠረቱ ቢሆኑም፣ ገዢው ፓርቲ እና ከተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል አንዱ እና ትልቁ የተደራጁት በብሔር ላይ በመመስረት አልነበረም።

የብሔር፣ የዘር ወይም የጎሳ አናሳዎች ወይም ቡድኖች አባላት የተጎዱባቸው በርካታ የማኅበራዊ ጥቃት ክስተቶች ነበሩ። በአማራ ክልል በተሰጠ መግለጫ መሠረት በሐምሌ ወር ማንነታቸው ያልታወቀ ታጣቂዎች በቤኒሻጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት፣ መተከል ዞን፣ ጉባ ወረዳ በሚገኝ አንድ መንደር ላይ ጥቃት ከፍተው 14 የአማራ ብሔር ተወላጆችን ገደሉ። የአማራ ክልል አንድ ባለሥልጣን በዚህ "አስቀድሞ በታቀደ እና የብሔር ግጭት ለማስነሳት በታሰበ ጥቃት" ስድስት ግለሰቦች ጉዳት ደርሶባቸዋል ብለዋል። በመቀጠል ሐምሌ 30፣ ነሐሴ 1 እና 7 በመተከል ዞን በሚገኙ ሦስት የተለያዩ ስፍራዎች ጥቃቶች ተፈጸሙ። ይህ ጥቃት ከብቶችን መዝረፍ ፣ መንገደኞችን አድፍጦ ማጥቃት፣ ጥቃቶች፣

የቤተክርስቲያን ዘረፋዎችን ያካተተ ሲሆን፣ የ160 ሰዎችን ሞት አስከትሏል።በመሆኑም ጸጥታን ለማስከበር የአገር መከላከያ ኃይል መሰማራት ነበረበት።

ሰኔ 23 ቀን ታዋቂው እርቲስት እና አክትቪስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ከተገደለ በኋላ በሐረር እና በኦሮሚያ ክልል ልዩ ልዩ አካባቢዎች የኦሮሞ ወጣቶች ቤት ለቤት በመሄድ ኦሮሞ ባልሆኑ ላይ ጥቃት አድርሰው ንብረታቸውንም አወደሙ። አብዛኛው ረብሻ የተከሰተው ከሰኔ 23 እስከ ሰኔ 29 ባለው ጊዜ ነበር። ከሃጫሉ ሞት በኋላ በመላው የኦሮሚያ ክልል ኃይል የተሞላበት የአመጽ እንቅስቃሴ ተካሂዶከ170 በላይ ሰዎች ሲገደሉበርካታ ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ ንብረቶች ወደሙ። የፌዴራል እና የክልል ባለሥልጣናት በዚህ አመጽ ላይ ተሳትፈዋል ያሏቸውን 5,728 ሰዎች በቁጥጥር ስር በማዋል ምርመራ አካሂደዋል። ፖሊስ በዚህ አምጽ ውስጥ በግብረ-አበርነት የአካባቢ ባለሥልጣናትን እና ፖሊሶችን በቁጥጥር ስር አውሏል። (በክፍል 1.ሀ.፣ የሰዎችን ክብር መጠበቅ - በዘፈቀደ መብትን መከልከል የሚለውን ክፍል ይመልከቱ)።

በማዕከላዊ መንግሥት እና በትግራይ ክልል መንግሥት መካከል ውጥረቱ እየጨመረ ሲሄድ በጸጥታ ኃይሉ፣ በመንግሥት ሥራ ውስጥ ያሉ እና ሌሎች የትግራይ ተወላጆች በቁጥጥር ስር ዋሉ፣ ታሰሩ ወይም ሥልጣናቸውን እንዲለቁ አለበለዚያም ፈቃድ እንዲወስዱ መደረጋቸውን የሚገልጹ በርካታ ሪፖርቶች ነበሩ። ኅዳር 15 ቀን እና ታኅሳስ 16 ቀን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ በማይ ካድራ እና በዙሪያው ባሉ ከተሞች ጥቅምት 30 የተከሰቱ በብሔር ላይ የተመሠረቱ ግድያዎችን በማስመልከት ግምገማዎችን አውጥተዋል።ከጥቅምት 30ው ጥቃት አስቀድሞ የትግራይ ሚሊሽያ እና የክልሉ የጸጥታ ኃይሎች ጥቃት ከመፈጸማቸው በፊት የአማራ ተወላጆችን መታወቂያ ይጠይቁ ነበር። በዚህ ጥቃት ከ600 እስከ 1,200 ሰዎች ሞተዋል፤ በአቡነ አረጋዊ ቤተክርስቲያን አካባቢ ጅምላ መቃብር የተገኘ ሲሆን የግል ንብረቶችም ወድመዋል።

በወሲብ ዝንባሌና በጾታ ማንነት ላይ የተመሰረቱ የጥቃት፣ የመወንጀል እና ሌሎች የበደል ተግባራት

በስምምነት የሚፈፀም የተመሳሳይ ጾታ ወሲባዊ ተግባር ህገ ወጥ የሆነና ከሶስት እስከ 15 ዓመት እስር የሚያስቀጣ ነው። ሴት ከሴት ወሲብ በሚፈጽሙ፣ በግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት

ጾታ ባላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ባስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ባላቸው ግለሰቦች (LGBTI) ላይ የሚደረግን ማግለል የሚከለክል ህግ የለም። ሴት ከሴት ወሲብ በሚፈጽሙ፣ በግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት ጾታ ባላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ባስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ባላቸው ግለሰቦች ላይ ጥቃት መፈፀምን የሚያሳዩ ሪፖርቶች ነበሩ፣ ይሁን እንጂ ብቀላን፣ ማግለልን ወይም መጠቋቆምን በመፍራት ሪፖርት የማድረግ ሁኔታ ውሱን ነበር። ሴት ከሴት ወሲብ በሚፈጽሙ፣ በግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት ጾታ ባላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ባስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ባላቸው ግለሰቦች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ምርመራን በመደገፍ ረገድ የጥላቻ ወንጀል ህጎች ወይም ሌሎች ስለወንጀል ፍትሕ የአሰራር ዜዴዎች የሉም። ግለሰቦች በከባድ ማህበረሰባዊ መገለልን በስምምነት የሚፈፀም የተመሳሳይ ፆታ ወሲባዊ ተግባር ህገ ወጥነት ምክንያት ሴት ከሴት ወሲብ ፈጻሚዎች፣ ግብረሰዶማዊያን፣ ሁለት ጾታ ያላቸው ፍናፍንቶች፣ ፆታቸውን ያስቀየሩ፣ እና ህብረ ፆታዊነት ያላቸው ሰዎች በአብዛኛው ራሳቸውን አይገልጹም።የሴት ከሴት ጋር ወሲብ ፈጻሚዎች፤ የግብረሰዶማውያን፣ የባለ ሁለት ፆታ ፍናፍንቶች፤ የፆታ ቀያሪዎች እና የህብረት ፆታ ፈፃሚዎች ማህበረሰብ አቀንቃኞች/አክቲቪስቶች ክትትል እንደሚደረግባቸው ሪፖርት አድርገው ለደህንነታቸው እንደሚፈሩ ገልፀዋል። በፈቃደኝነት በተመሳሳይ ጾታ የወሲብ ተግባራት ውስጥ በመሳተፋቸው የታሰሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎች ስለመኖራቸው የሚገልጹ ሪፖርቶች የሉም።

አዲስ አበባ ያለው የኤይድስ ሪሶርስ (ግብዓት) ማዕከል ራሳቸውን ግብረሰዶማዊ ወይም ሴት ከሴት ጋር ወሲብ የሚፈፅሙ አድርገው የገለፁ እና አብዛኞቹ ወንዶች የሆኑ የስልክ ደዋዮች ባህርያቸውን በመለወጥ መገለልን ለማስቀረት ድጋፍ መጠየቃቸውን ሪፖርት አድርጓል። ብዙዎች ግብረሰዶማዊያን መበርገግ ፣ ግራ መጋባት፣ የማንነት ቀውስ፣ ጭንቀት፣ ራስን ማግለል፣ ሐይማኖታዊ ግጭትና ራስን የማጥፋት ሙከራዎች እንደገጠማቸው ሪፖርት አድርገዋል።

ኤችአይቪ እና ከኤድስ ጋር የተገናኘ ማህበራዊ መገለል

በኤችአይቪ/ኤድስ በተጠቁ ሰዎች ላይ የሚያጋጥም ማህበራዊ መገለልበትምህርት፣ በቅጥር፣ እና በማህበረሰብ ውህደት ዙሪያ ቀጥለዋል። በኤችአይቪ ወይም በኤይድስ

የተጠቁ ሰዎች ወደ በርካታ አገልግሎቶች ለመዳረስ መቸገራቸውን ሪፖርት አድርገዋል። በችግሩ መጠን ላይ አሀዛዊ መረጃዎች የሉም።

ሌላ ማህበራዊ ጥቃት ወይም መድልዎ

በሚያዝያ ወር በኮቪድ-19 ምክንያት የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች የተዘጉ ቢሆንምዩኒቨርሲቲዎቹ ቀድሞውኑ የብሔር ማንነት በወለደው ውጥረት የአመጽ እና የጥቃት ማዕከል ሆነው የከፋ የትምህርት መቋረጥ አስከትሏል። ሴንተር ፎር አድቫንስመንት ኦፍ ራይትስ ኤንድ ዴሞክራሲ (የመብቶች እና የዲሞክራሲ ዕድገት ማዕከል) የተባለ የአገር ውስጥ የመብቶች ቡድን እንዳለው በቀድሞው ዓመት (ከመስከረምእስከ መጋቢት ወር 2012) በአገሪቱ ከሚገኙ 45 የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች በ28ቱ 12 ተማሪዎች ሕይወታቸውን ሲያጡ ከ58 በላይ የሚሆኑት ደግሞ ጉዳት ደርሶባቸዋል። ሪፖርቱ እንዳለው አብዛኛው ረብሻ ከብሔር ጋር የተያያዘ ሆኖ ነገር ግን መነሻ ምክንያቶች ይለያያሉ፤ አንዳንዶቹ የተነሱት በግለሰቦች መካከል በሚፈጠር ጠብ ነበር። ይህንንም ተከትሎ መንግሥት ግድያ ፈጽመዋል ተብለው የተጠረጠሩ 15 ተማሪዎች እና ሁለት የአስተዳደር ሠራተኞችን በቁጥጥር ሥር አውሏል። በተጨማሪም መንግስት ሶስት የዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዝዳንቶችን፣ አራት ፕሮፌሰሮችን እና አንድ የጤና መኮንንን በረብሻው ውስጥ ተሳትፋችኋል በማለት በጊዜያዊነት ወይም በዘላቂነት አግዷቸዋል። ከፍተኛው ረብሻያጋጠመው በወሎ ዩኒቨርሲቲ፣ አማራ ክልል ሲሆን፣ በዚህ ዩኒቨርሲቲ ለሦስት ጊዜያት ያህል ረብሻ አጋጥሟል።

ክፍል 7፡ የሰራተኛ መብቶች

ሀ. የመደራጀት ነጻነት እና የሕብረት ድርድር የማድረግ መብት

ህገ መንግስቱ እና ህጉ ከመንግስት ሰራተኞችና በቀዳሚነት በተወሰኑ ፈርጆች ማለትም በዋናነት በጤናው ዘርፍ ውስጥ ካሉ አንዳንድ የሰራተኞች ምድቦች በስተቀር ማህበራትን የመመስረትና አባል የመሆን፣ ህጋዊ የስራ ማቆም እንዲሁም ሕጋዊ አድማ የማድረግና የህብረት ድርድር የማካሄድ መብትን ለሰራተኞች ይሰጣሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሌሎች ድንጋጌዎችና ህጎች እነዚህን መብቶች በጣም ይገድባሉ። በተለይም ህጉ የአስተዳደር ሰራተኞችን፣ መምሕራንን ፣ የጤና እንክብካቤ ሰራተኞችን፣ ዳኞችን፣ አቃቤ ህጎችን፣

የደህንነት አግልገሎት ሰራተኞችን፣ የቤት ሰራተኞችን እና በወቅት ላይ የተመሰረተ የግብርና ስራ የሚያካሄዱ ሰራተኞችን በማህበራት መደራጀትን ይከለክላል።የጸረ-ማህበር ማግለልን በመፈፀም ጥፋተኛ የሆኑ አሰሪዎች በማህበር የስራ እንቅስቃሴዎች ምክንያት የተሰናበቱ ሰራተኞችን ወደ ስራ ገበታቸው እንዲመልሱ ህጉ ያስገድዳል።

አንድን ማህበር ለመመስረት ቢያንስ 10 ሰራተኞች ያስፈልጋሉ። ሕጉ ሁሉም የሠራተኞች ማኅበራት የመመዝገብ መብት እንዳላቸው የሚደነግግ ቢሆንም፣ መንግሥት የምዝገባ መስፈርቶች የማያሟሉ ማኅበራትን ላይመዘግብይችላል። የማኅበር መሪዎች በፍርድ ቤት ሕዝባዊ መብቶቻቸው የተገደበ ከሆነ እና ማኅበሩም አነርሱን ለመተካት እምቢተኛ ከሆነ የምዝገባ ጥያቄያቸው ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል። ነገር ግን በዚህ መነሻነትየምዝገባ ጥያቄ ውድቅ ስለመደረጉ የቀረበ ዘገባ የለም። መንግሥት የአንድን ማኅበር ምዝገባ በራሱ ውሳኔ ሊሰርዝ ይችላል። ሠራተኞች በእያንዳንዱ የቅጥር ጊዜያቸው ከአንድ በላይ የሠራተኞችማኅበር ውስጥ አባል ሊሆኑ አይችሉም። ሕጉ እንደሚደነግገው አንድ የሠራተኛ ማኅበር በግልጽ እንደ ፖለቲካ ድርጅት ሊንቀሳቀስ አይችልም።

በሕጉ የአስተዳደር አካላት በፍርድ ቤት አማካኝነት በተከለከለ ተግባር ለምሳሌ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፉ ማኅበራት እንዲሰረዙ ለፍርድ ቤት ጥያቄ እንዲያቀርብይፈቅዳል።

ህጉ ለሕብረት ድርድር መብት እውቅና ቢሰጥም፣ ይህ መብት በህጉ መሰረት በጥብቅ ተገድቧል። የጋራ ድርድር ስምምነትን ለማሻሻል ወይም ለመተካት ያለሙ ድርድሮች ጊዜው ባበቃ በሶስት ወራት ውስጥ መከናወን አለባቸው፤ አለበለዚያ በምንዳዎች እና በሌሎች ጥቅማጥቅሞች ላይ የበፊቶቹ ድንጋጌዎች መተግበራቸው ያቆማል። የድርጅት ማህበራት በምንዳ ክፍያ ላይ በፋብሪካ/ኢንዱስትሪ ደረጃ ብቻ እንዲደራደሩ ህጉ ይደነግጋል። የመንግስት ት/ቤት አስተማሪዎችን ጨምሮ የመንግስት ሰራተኞች በተቀጣሪ ሰራተኞች የተቋቋሙ የሙያ ማህበራትን የመመረስትና አባል የመሆን መብት ቢኖራቸውም የሕብረት ድርድር ማድረግ አይችሉም። በመንግስት ዘርፍ ውስጥ የግልግል (አርቢትሬሽን) የአሰራር ሥርአቶች ከግሉ ዘርፍ ይልቅ የበለጠ አጋጅ ናቸው። በሕግ ጥሰት ምክንያት የሚጣሉ ቅጣቶች ለተመሳሳይ ወንጀሎች ከሚጣሉት ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም።

ሰራተኞች ጥቅሞቻቸውን ለማስከበር የሥራ ማቆም አድማ እንዲያደርጉ ህገ መንግስቱና ህጉ ቢደነግጉም ህጋዊ ስራ የማቆም አድማ ተግባራትን በሚያግድ መልኩ አስቸጋሪ የሚያደርጉ በጣም ውስብስብና ጊዜ የሚፈጁ ሥነ-ሥርዓቶችን የሚያዙ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ይይዛል። ተበዳይ ሰራተኞች የሥራ ማቆም አድማ ከማድረጋቸው በፊት ከአሰሪዎች ጋር ለመታረቅ እንዲሞክሩ ህጉ የሚያዝ ሲሆን እንዲሁም ረዥም የክርክር እልባት መስጫ ሂደትን ያካትታል። እነዚህ ድንጋጌዎች አሰሪዎች ሰራተኞችን ወደ መስሪያ ቤት እንዳይገቡ ለማገድ ባላቸው መብት ላይም በእኩል ደረጃ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ፈቃድ ላለው የስራ ማቆም አድማ ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ሁለት ሶስተኛው እንዲህ አይነቱን እርምጃ መደገፍ አለባቸው። ጉዳዩ ወደ ፍ/ቤት ወይም ወደ አሰሪና ሰራተኛ ግንኙነቶች ቦርድ ካልተመራ፣ ማህበሩ ወደ እነዚህ ሁለት አማራጮች መሄድ ሳያስፈልገው የስራ ማቆም አድማ የማድረግ መብትን ይይዛል፤ ይህ የሚሆነው ግን ለሌላው ወገን እና ለአሰሪና እና ለማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ቢያንስ የ10 ቀናት ማሳሰቢያ ከሰጡና በእርቅ ጉዳይ ላይ ጥረቶች ካደረጉ ነው።

በተጨማሪም ህጉ የአየር ትራንስፖርትና የአውቶብስ አገልግሎቶችን፣ የኤሌክትሪክ ሐይል አቅራቢዎችን የነዳጅ ማደያ ሰራተኞችን የሆስፒታልና ፋርማሲ ሰራተኞችን፣ የእሳት አደጋ ተከላካዮችን፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ሰራተኞችንና የከተማ ውስጥ የጽዳት ሰራተኞችን ጨምሮ መሰረታዊ አገልግሎቶች በሚሰጡ ሰራተኞች የሚደረጉ የስራ ማቆም አድማዎችን ያግዳል። የመሰረታዊ አገልግሎቶች ዝርዝር የዓለምአቀፍ ሰራተኞች ድርጅት (ILO) ስለ መሰረታዊ አገልግሎቶች ከሰጠው ፍቺ አልፎ የሚሄድ ነው። በአድመኞች ላይ ብቀላ እንዳይደረግ ህጉ ቢከለክልም ያልተፈቀዱ የስራ ማቆም እርምጃዎችን በማካሄዳቸው ጥፈተኛ በሆኑ ማህበራትና ሰራተኞች ላይ የፍትሐ ብሔርና የወንጀል መቀጫዎች መጣልን ጭምር ይደነግጋል። የወንጀለኛ መቅጫው ህግ ድንጋጌዎች ተጨማሪ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘ ተከሳሽ ላይ ክብደት ያላቸው መቀጫዎችን የሚያዙ ከሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ የተተረጎመው ቅጣት ተፈፃሚ ይሆናል። መንግስትን፣ ህዝብን ወይም የግል ጥቅሞችን በሚጎዳ ሁኔታ የሥራ ማቆም አድማ የሚያደርግ፣ ሌሎችን አድማ እንዲያደርጉ የሚገፋፋ ወይም ስራውን በትክክለኛ ሁኔታ የማያከናውን ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ የጉልበት ስራን የመስራት ግዴታ ለሚያካትት እስር ተገዢ ይሆናል።

አሠሪ የሠራተኛ ማኅበር ቀስቃሾችን (አክቲቪስቶችን) ከሥራ ስለማገዱ የቀረቡ ዘገባዎች የሉም። መደበኛ ያልሆነው የሥራ ዘርፍ፤ የቤት ሰራተኞችንና በወቅት ላይ የተመሰረተ የግብርና ስራ የሚሰሩ ሰራተኞችን ጨምሮ መደበኛ ያልሆነ የጉልበት ስራ ዘርፍ በማህበር አይደራጅም ወይም በአሰሪና ሰራተኛ ህጎች ከለላ አይሰጠውም። ህጉ ሰራተኞችን በስራ ቅጥር ግንኙነት ውስጥ እንዳሉ ሰዎች ይተረጉማቸዋል። የሠራተኞች በበቂ ሁኔታ አለመኖር መንግስትን የህግ ከለላ ላገኙ ዘርፎች ተፈጻሚ ህጎችን በስኬት ከማስከበር አግዶታል። የፍ/ቤት የአሰራር ሥርዓቶች ብዙውን ጊዜ ለተራዘሙ መዘግየቶችና ይግባኞች ተገዢ እየሆኑ ነው። ከፍተኛ የሥራ አጥነት፣ የብቀላ ፍራሐት እና የአሰሪና ሰራተኛ ክሶችን ችሎት ለመስማት የሚያጋጥሙ የተንዛዙ መዘግየቶች ሰራተኞችን በስራ ማቆም አድማዎች ወይም በሌሎች የሰራተኛ እርምጃዎች ከመሳተፍ እንዳገዳቸው የአሰሪና ሰራተኛ ሃላፊዎች ሪፖርት አድርገዋል።

ሁለት ሶስተኛው የማህበር አባላት መንግሥት ከሚቆጣጠረው የኢትዮጵያ የንግድ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን ጋር ግንኙነት ያላቸው ድርጅቶች አካላት ናቸው። መንግሥት የብሔራዊ መምህራን ማኅበርን የምዝገባ ሂደት አላካሄደም።

ለ. አስገዳጅ ወይም የግዴታ የጉልበት ስራ ክልከላ

ህጉ ሁሉንም ዓይነት የግዴታ ወይም አስገዳጅ የጉልበት ስራን የሚከለክልና በወንጀል የሚያስጠይቅ ቢሆንም ፍ/ቤቶች እንደቅጣት እርምጃ በማድረግ አስገዳጅ የጉልበት ስራን እንዲያዙ ይፈቅድላቸዋል።መንግስት በተሳካ ሁኔታ ህጉን ያላስከበረ በመሆኑ አስገዳጅ የጉልበት ስራ አጋጥሟል።

ምክር ቤቱ በሚያዝያ ወር ስለ ሰዎች ሕገ ወጥ ዝውውር እና ሰዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ማስተላለፍን የሚመለከት አዋጅ አወጣ። ሕጉ በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር እና በብዝበዛ፣ በባርነት፣ ሰዎችን አስገድዶ በማሰራት፣ በዕዳ ቀንበር፣ በግዴታ ለሴተኛ አዳሪነት በማሰማራት እና ሰዎችን ለግዞት በመዳረግ ጥፋተኛ ሆነው በተገኙ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ቅጣት ይጥላል። እነዚህ ቅጣቶች ከሌሎች ተመሳሳ ጥፋቶች ጋር ተመጣጣኝነት ያላቸው ናቸው። በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ፖሊስ በሰዎች ሕገ ወጥ ዝውውር እና በብዝበዛ ላይ ያተኮረ ሥልጠና ወስደዋል።

ብዙውን ጊዜ በአስገዳጅ ድርጊት ስር ያሉ አዋቂዎችና ልጆች በጎዳና ላይ ንግድ፣ በልመና፣ በእጅ በሚሸመኑ የባህላዊ የሽመና ስራ ጨርቆች ወይም በግብርና ስራ ላይ ተሰማርተዋል። እንዲሁም ልጆች በአስገዳጅ የቤት ውስጥ የጉልበት ስራ ይሰራሉ።

መንግስት አንዳንድ ጊዜ እስረኞችን ከማረሚያ ቤቶች ውጭ ለግል ድርጅቶች እንዲሰሩ የሚያሰማራ ሲሆን፣ ይህንን ድርጊት የአለምአቀፍ አሰሪና ሰራተኛ ድርጅት እንደ አስገዳጅ የጉልበት ስራ መውሰድ ይቻላል ብሏል።

በhttps://www.state.gov/trafficking-in-persons-report/ላይ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የሰዎችን ህገ-ወጥ ዝውውር ሪፖርት ጭምር ይመልከቱ።

ሐ. የሕፃናት የጉልበት ስራ ክልከላ እና አነስተኛው የሥራ ቅጥር እድሜ

ህጉ በጣም አስከፊ የሆኑ ማንኛቸውንም አይነቶች የሕፃን ልጅ የጉልበት ሥራ ይከለክላል። መንግስት አግባብነት ያላቸውን ህጎች በተሳካ ሁኔታ ያልተገበረ ሲሆን መቀጫዎችም ተነጻጻሪ ለሆኑ ጥፋቶች ከሚጣሉት ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም።

በመስከረም 2012 የጸደቀው ሕግ አነስተኛው የሥራ ቅጥር ዕድሜ ከ14 ዓመት ወደ 15 ዓመት እንዲያድግ አደረገ።
አነስተኛ የእድሜ ድንጋጌዎች ግን በውለታ/በኮንትራት ለሚሰሩ ሰራተኞች ብቻ እንጂ እጅግ ብዙ የስራ ቅጥር ህፃናትን በሚያካትቱ በግላቸው በተቀጠሩ ወይም የማይከፈልበት ስራ በሚሰሩ ልጆች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም። እድሜያቸው ከ15 እስከ 18 የሆኑ ህጻናት አደገኛ ወይም የሌሊት ስራ መስራትን ህጉ ይከለክላል። የህጻን ልጅን ጤንነት አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ማንኛውም ስራ እንደአደገኛ ስራ ሆኖ በህግ ይተረጎማል። የተከለከሉ የሥራ ዘርፎች የመንገደኛ ማጓጓዣ ትራንስፖርትን፣ በኤሌክትሪክ ሐይል ማመንጫ ኢንዱስትሪዎች መስራትን፣ የፋብሪካ ስራን፣ ከመሬት ወለል በታች መስራትን፣ ጎዳና ማጽዳትን እና ሌሎች ብዙ ዘርፎችን ያካትታሉ። አደገኛ ተንቀሳቃሽ እና ሌሎች መሳሪያዎች አገልግሎት የሚሰጡበት ልማዳዊ የሽመና ሥራ በአደገኛ ሥራ ገደቦች ውስጥ አይጠቃለልም። እድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች ሆኖ በሙያ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ልጆች ህጉ ከአደገኛ ስራ በጥብቅ ያገልላቸዋል። ከ15 እስከ 18 እድሜ ያላቸው ልጆች በቀን ከሰባት

ሰዓታት በላይ እንዲሁም ከምሽቱ 4:00 እስከ ጠዋቱ 12:00 ሰዓት ወይም በበዓላት ቀናት ወይም በእረፍት ቀናት እንዲሰሩ ህጉ አይፈቅድም።

የሕጻናት የጉልበት ስራ ከባድ ችግር ሆኖ ቆይቷል (በተጨማሪ ክፍል 7. ለን ይመልከቱ ፣ የሠራተኞች መብቶች -- አስገድዶ ማሰራት ወይም የግዴታ ሥራ ክልከላ) እናም በርካታ ቁጥር ያላቸው ህጻናት በተከለከሉ፣ እና አደገኛ በሆኑ በተለይ በግንባታው ዘርፍ ይሰራሉ።

ልጆች በገጠር እና በከተማ አካባቢዎች አዘውትረው ይሰሩ ነበር። በተለይ በሕይወት ማቆያ የግብርና ምርት ስራ፣ በባህላዊ ሽመና፣ በአሳ ማጥመድ እና በቤት ውስጥ ስራ የህጻን ልጅ የጉልበት ስራ ተስፋፍቶ ይገኛል። ዕድሜያቸው ከ8-17 የሆነ በሺዎች የሚቆጠሩ ልጆች በጫት ምርት ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ ተዘግቧል። ቁጥራቸው እያደገ የመጣው ልጆች በግንባታ ሥራ ላይ ተሰማርተዋል። በገጠር አካባቢዎች ያሉ ህጻናት በተለይም ወንዶች ልጆች በከብት እረኝነት፣ ጥቃቅን እቃዎችን በመሸጥ፣ በአጨዳ እና አረም መንቀልን በመሳሰሉ ተግባራት ውስጥ የሚሳተፉ ሲሆን ሴቶች ልጆች ደግሞ ማገዶ በመልቀም እና ውሃ በመቅዳት ላይ ተጠምደዋል። ልጆች የወርቅ ማዕድን ቁፋሮ ሥራ ይሰራሉ። በአነስተኛ ደረጃ በሚካሄድ የወርቅ ማዕድን ስራ የማዕድን ጉድጓዶችን ይቆፍራሉ እንዲሁም ከባድ የውሃ ጭነቶችን ይሸከማሉ: ወላጅ አልባ ልጆችን ጨምሮ በከተማ አካባቢዎች ያሉ ህጻናት በርካታዎቹ ብዙውን ጊዜ ለረጅም ሰዓታት በመሥራት የቤት ውስጥ አገልግሎት ስለሚሰጡ ትምህርታቸውን አዘውትረው እንዳይከታተሉ ያደርጋቸዋል። እንዲሁም ልጆች በማምረቻ ቦታዎች፣ ጫማ በመወልወል፣ ልብስ በመስፋት፣ መኪና በመጠበቅ፣ በህዝብ ትራንስፖርት፣ በጥቃቅን ንግድ፣ በተሸካሚነት እና የታክሲ ተራ በማስያዝ ይሰራሉ። አንዳንድ ልጆች በአነስተኛ ክፍያ ወይም ምንም ሳይከፈላቸው እና የስራ ላይ የደህንነት መጠበቂያ መሳሪያዎች ሳይኖራቸው በአደገኛ ከባቢ-ሁኔታዎች ውስጥ ለረጅም ሰዓታት ይሰራሉ። ህጻናት የጉልበት ሰራተኞች አካላዊ፣ ወሲባዊ እና ስሜታዊ ጥቃትን የመሳሰሉ በደሎች በአሰሪዎቻቸው ይደርስባቸዋል።

ህገ-ወጥ የሰው አዘዋዋሪዎች ድህነት ከተንሰራፋባቸው የገጠር አካባቢዎች ልጃገረዶችን በመበዝበዝ በዋናነት በቤት ውስጥ የባርነት አገልግሎት እና በሐገሪቱ የወሲብ ንግድ ውስጥ ያሰማሯቸዋል።

በhttps://www.dol.gov/agencies/ilab/resources/reports/child-labor/findings ላይ በጣም በከፉ የህጻን ልጅ ጉልበት ብዝበዛዎች ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን የጉልበት ስራ ግኝቶችን ጭምር ይመልከቱ።

መ. ከቅጥር እና ከሥራ ጋር በተያያዘ ማግለል

ህጉ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በጾታ፣በትዳር ሁኔታ፣ በሐይማኖት፣ በፖለቲካ ትስስር፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በእርግዝና፣ በማህበረ ኢኮኖሚ ደረጃ፣ በአካል ጉዳተኝነት፣ ወይም በ "ማናቸውም ሌሎች ሁኔታዎች" ላይ ተመስርቶ የሚደረግ ማግለልን ይከለክላል።ቅጥርንና የሥራ አይነትን አስመልክቶ ህጉ ማግለልን ይከለክላል፣ ይሁን እንጂ ባለስልጣናት እነዚህን መብቶች በስራ ላይ የሚያውሉት በተዛባ ሁኔታ ነው ። ህጉ ነፍሰ ጡር ሴቶችና በአካል ጉዳተኞች ላይ ላለ ተጨማሪ ጫና ልዩ እውቅናን ይሰጣል። ከላይ በተጠቀሱት ማናቸውም ምክንያቶች ላይ ለሚደረግ ማግለል የጥፋተኝነት መቀጫ ከሌሎች ተነጻጻሪ ጥፋቶች ጋር ተመጣጣኝ አይደለም። መንግስት ህጉን ለማስከበር ውስን እርምጃዎችን ወስዷል። የወሲብ ዝንባሌ፣ የጾታ ማንነት እና የኤችአይቪ በደም ውስጥ መገኘት በህጉ መሰረት ከለላ ለማግኘት መሰረት የላቸውም።

የሴቶችን ቅጥር በተመለከተ ለምሳሌ አደገኛ ናቸው ተብለው በሚቆጠሩ ሥራዎች ሴቶች እንዳይሳተፉ በሕግ የተቀመጡ ገደቦች ያሉ ሲሆን እነርሱ ማዕድን ማውጣት እና ግብርናን ያካትታሉ። ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች ሥራ የማግኘት ዕድሎች አናሳ ናቸው። ለእኩል ሥራ እኩል ደመመዝ እንዲከፈል ሕጉ አያስገድድም፤ ያሉትም ሥራዎች በዚህ መልኩ ሴቶችን አያስተናግዱም። በጾታ ግንኙነት ምርጫ እና በጾታ ማንነት ምክንያት በቅጥር ዕድል እና ሥራ ላይ አሁንም መድልዎ ያጋጥማል።

እ.ኤ.አ. በ2019 የሰደተኞች አዋጅ ከጸደቀ በኋላ ስደተኞች ሥራ ላይ ለመሰማራት ያላቸውን መብት ለመወሰን መንግሥት በሰኔ ወር መመሪያ አውጥቷል። የመስራት መብት መመሪያው ስደተኞች እና የፖለቲካ ጥገኝነት ጠያቂዎች ስደተኞችን እና ዜጎችን በሚጠቅሙ በዓለም ዓቀፉ ማኅበረሰብ ድጋፍ በሚደረግላቸው የልማት ፕሮጀክቶች ላይ እንዲሳተፉ ወይም በግል ሥራ ገቢ እንዲያገኙ ይፈቅዳል።

ሰ. ቅቡልነት ያላቸው የስራ ሁኔታዎች

በብሔራዊ ደረጃ የተቀመጠ አነስተኛ የክፍያ ተመን የለም። አንዳንድ የመንግስት ተቋማት እና የመንግስት ድርጅቶች የየራሳቸውን አነስተኛ ክፍያዎች ይወስናሉ። በቁጥር ከፍተኛ የደመወዝ ተከፋይ ቡድን የሆኑ የመንግስት ዘርፍ ሰራተኞች በወር ከድህነት መስመር በላይ የሆነ አነስተኛ ክፍያ ያገኛሉ።

ህጉ ከ24 ሰዓት የእረፍት ጊዜ ጋር ቢበዛ የ48-ሰዓት ሀጋዊ የስራ ሳምንት፣ ለትርፍ ጊዜ ስራ ተጨማሪ ክፍያ እንዲከፈል፣ እና በግዴታ የሚሰራ ተጨማሪ የትርፍ ጊዜ ስራ እንዳይኖር ይደነግጋል። አሰሪዎች የትርፍ ሰዓት ስራን ለመጠቀም የሚችሉባቸው 4 ሁኔታዎች አሉ። እነርሱም፡- የስራው አስቸኳይነት፣ አደጋ፣ የሰራተኛ መቅረት፣ እና የአማራጮች እጦት ናቸው። በተጨማሪ አሰሪዎች በቀን ከሁለት ሰዓታት፣ በወር ከ20 ሰዓታት እና በዓመት ከ100 ሰዓታት ለሚበልጥ ጊዜ ሰራተኞቻቸውን የትርፍ ሰዓት ስራ ማሰራት አይኖርባቸውም። ህጉ በህዝብ ድርጅቶች እና በመንግስት የፋይናንስ ተቋማት የሚሰሩ ሰራተኞች የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲያገኙ መብት ይሰጣቸዋል፤ የመንግስት ሰራተኞች ለትርፍ ሰዓት ስራ ማካካሻ የሚሆን የእረፍት ጊዜ ይሰጣቸዋል። በጠቅላላው፣ መንግሥት ደመወዝን የሚመለከቱ ሕግጋትን በውጤታማነት አልተገበረም። የተጣሉትም ቅጣቶች በተመሳሳይ ወንጀሎች ላይ ከሚጣሉት ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም።

መንግስት፣ ኢንዱስትሪዎች እና ማህበራት በብዙ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ለሰራተኛ ደህንነት ሙሉ መፍትሔ በማይሰጡ የስራ ላይ ደህንነትና የጤና ደረጃዎች ላይ ተደራድረዋል። የቤት ሰራተኞችን እና በወቅት ላይ የተመሰረተ የግብርና ሰራተኞችን ጭምር የሰራተኞች ማህበር ከመመስረት በተለየ ሁኔታ በህግ ይከለከላሉ። በአጠቃላይ በስራ ቦታ የጤና እና የደህንነት ጥበቃ ደንቦች ተጠቃሚ አልሆኑም።የሚሰጡ ቅጣቶችም በተመሳሳይ ወንጀሎች ላይ ከሚጣሉት ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም።

የአሰሪና ሰራተኞች ሚኒስቴር የኢንስፔክሽን መምሪያ የስራ ቦታ ደረጃዎችን የማስከበር ሃላፊነት ነበረበት። የሥራ ላይ ደህንነት እና የጤና እርምጃዎች በተጠናከረ ሁኔታ ስራ ላይ አልዋሉም። ሚኒስቴር መ/ቤቱ ደንብ የመከበር አፈጻጸምን ለመከታተል የሰራተኛ ቁጥጥሮችን ያካሄደ ቢሆንም መንግስት ህጉን ለማስከበር በቂ የተቆጣጣሪዎች ብዛት አልነበረውም። የሚኒስቴር መ/ቤቱ የአስተዳደር ብቃት ውሱንነት፤ የመቀበል፣

የመመርመር፣ እና የጥሰት ውንጀላዎችን የመከታተል ውጤታማ ስልት ያለመኖር እንዲሁም ዝርዝር መረጃን የያዙ ዘርፍ-ተኮር የጤና እና የደህንነት መረጃዎች ጉድለት የነዚህን ደረጃዎች ስኬታማ ተግባራት አደናቅፈዋል። የሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2010 46,000 ምርመራዎችን ያጠናቀቀ ሲሆን አስተማማኝነት የሌላቸውን ሁኔታዎች ለይቶ የማወቁ ሃላፊነት በሰራተኛ ተቆጣጣሪዎች ላይ ማረፉ ግልፅ ነበር።

በክፍያ-ሰራተኛነት ቅጥር ውስጥ ተሳታፊ የሆነው በከተሞች አካባቢ የተከማቸው የህዝቡ አነስተኛ መቶኛ መጠን ያህሉ ብቻ ነው። መደበኛ ባልሆነ ዘርፍ ውስጥ የሚፈፀሙ ክፍያዎች በአብዛኛው ሕይወትን ከማቆያ ደረጃዎች በታች ናቸው።

በወቅት ላይ የተመሰረቱ የግብርና ሰራተኞች የካሳ ክፍያ፣ ጥቅማጥቅሞች እና የሥራ ሁኔታዎች በማህበር ከታቀፉ ቋሚ የግብርና ተቀጣሪ ሰራተኞች እጅግ ያነሱ ናቸው። መንግስት ህጉን ለማስከበር የፈፀመው ተግባር አነስተኛ ነው። በመደበኛው ዘርፍ አብዛኞቹ ሰራተኞች በሳምንት 39 ሰዓታት ነው የሚሰሩት። ብዙዎቹ የውጭ ሐገር፣ የሥደተኛ እና መደበኛ ያልሆኑ የጉልበት ሰራተኞች በሳምንት ከ48 ሰዓታት በላይ ይሰራሉ።

የሐገሪቱ ኢኮኖሚ ዋነኛ መሰረት በሆነው የግብርና ዘርፍ ውስጥ አደገኛ የስራ ሁኔታዎች አሉ። ስለ ሞት እና ጉዳቶች የሚገልፁ መረጃዎች ባይገኙም በግንባታና በኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ አደገኛ እና በዝባዥ የሥራ ሁኔታዎች እንዳሉ የሚገልፁ ሪፖርቶችም አሉ።